# የእግዚአብሔር መጋቢነት

በተጨማሪ መጽናናትን በገጽ 46፣ መታመንን በገጽ 224 ላይ ተመልከቱ።

1. እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ሁሉንም ነገሮች እንደ ፈቃዱ ያደርጋል።

   ኤፌ. 1:11። ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል።

2. የእግዚአብሔር ሉዓላዊ አገዛዝ ሁሉንም ነገሮች ይጠቀልላል።

   መዝ. 103:19። እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አጽንቶአል፤ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።

   ሐዋ. 17:28። የምንኖረውና የምንንቀሳቀሰው፣ ያለነውም በእርሱ ነውና። ከራሳችሁ ባለቅኔዎችም አንዳንዶቹ እንዳሉት፣ <እኛ ደግሞ ልጆቹ ነን>።

   ሮሜ 11:36። ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

3. እግዚአብሔር ለወፎችና ለአበቦች ይጠነቀቃል፣ ለልጆቹ ደግሞ በእርግጥ ይበልጥ ይጠነቀቃል።

   ማቴ. 6:25-34።

   ማቴ. 6:26። እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም፤ አያጭዱም፤ በጐተራም አያከማቹም፤ ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል። እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን?

   ማቴ. 6:30። እናንተ እምነት የጐደላችሁ! እግዚአብሔር ዛሬ ታይቶ በነጋታው እሳት ውስጥ የሚጣለውን የሜዳ ሣር ይህን ያህል ባለበሰ እናንተንማ እንዴት አብልጦ አያለብሳችሁ?

4. ኣግዚአብሔር ሁሉንም የተፈጥሮ ኀይላት ይቆጣጠራል እንዲሁም ፍጥረቱን ሁሉ ይመግባል፣ በተለይም ለልጆቹ ይህን አብልጦ ያደርጋል።



   መዝ. 104፤ መዝ. 145፤ መዝ. 147።

5. እግዚአብሔር ኤልያስን ለመንከባከብ ቁራዎችን ተጠቀመ።

   1ኛ ነገ. 17:16።

   1ኛ ነገ. 17:4-5። ውሃ ከወንዙ ትጠጣለህ፤ ቍራዎችም እዚያው እንዲመግቡህ አዝዣለሁ።» ስለዚህ እግዚአብሔር ያዘዘውን ፈጸመ፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ወዳለው ወደ ኮራት ወንዝ ሄዶ በዚያ ተቀመጠ። ቍራዎችም ጧትና ማታ እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፤ ውሃም ከወንዙ ይጠጣ ነበር።

6. በእያንዳንዱ ቀን ከሰማይ መናን በመስደድ፣ እግዚአብሔር ታማኝነቱን፣ ኃይሉንና ፍቅሩን ገለጠ።

   ዘፀ. 16።

7. እግዚአብሔር ሸክላ ሠሪው ነው፣ እኛ ደግሞ ሸክላዎቹ ነን። ስለዚህ ለእርሱ ተገዙ።

   ኤር. 18:1-10።

   ኤር. 18:5-6። የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፤ «የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ሸክላ ሠሪው እንደሚሠራው፣ እኔ በእናንተ ላይ መሥራት አይቻለኝምን?» ይላል እግዚአብሔር፤ «የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ጭቃው በሸክላ ሠሪው እጅ እንዳለ፣ እናንተም እንዲሁ በእጄ ውስጥ ናችሁ።»

   ኢሳ. 45:9-13።

   ኢሳ. 45:9-11። «ከዐፈር ሸክላዎች መካከል፣ ከሠሪው ጋር ክርክር ለሚገጥም ወዮለት፤ ጭቃ፣ ሸክላ ሠሪውን፣ <ምን እየሠራህ ነው?> ይለዋልን? የምትሠራውስ ሥራ፣ <እጅ የለህም> ይልሃልን? አባቱን፣ <የወለድኸው ምንድን ነው?> ለሚል፣ እናቱንም፣ <ምን ወለድሽ>? ለሚል ወዮለት። «የእስራኤል ቅዱስ፣ ሠሪውም የሆነ እግዚአብሔር፣ ስለሚመጡ ነገሮች እንዲህ ይላል፤ <ስለ ልጆቼ ትጠይቁኛላችሁን? ስለ እጆቼስ ሥራ ታዝዙኛላችሁን?>»

8. እግዚአብሔር ለልጆቹ ያለውን ዓላማ ለመፈጸም ክፉ ገዢዎችን ይጠቀማል።

ኢሳ. 45:12-13:: <ምድርን የሠራሁ እኔ ነኝ፤ ሰውንም በላይዋ ፈጥሬአለሁ፤ እጆቼ ሰማያትን ዘርግተዋል፤ የሰማይንም ሰራዊት አሰማርቻለሁ:: ቂሮስን በጽድቅ አስነሥቻለሁ፤ መንገዱን ሁሉ አስተካክዬለታለሁ፤ ከተማዬን እንደ ገና ይሠራታል፤ ምርኮኞቼን ያለ ክፍያ ወይም ያለ ዋጋ፣ ነጻ ያወጣል፤> ይላል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር::

*ዕዝራ 7:1-10:: (እግዚአብሔር፣ ዕዝራ የጠየቀውን ነገር እንዲያደርግለት ንጉሥ አርጤክስስን ገፋፍቶታል:: ምክንያቱም «የእግዚአብሔር የአምላኩን እጅ በእርሱ ላይ ነበረች::»)*

*ዕዝራ* 7:6:: ይህ *ዕዝራ* ከባቢሎን *መጣ*:: እርሱም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን ሕግ በሚገባ የሚያውቅ የሕግ መምህር ነበር:: የአምላኩ የእግዚአብሔር እጅ በእርሱ ላይ ስለ ነበረች፣ የጠየቀውን ሁሉ ንጉሡ ፈቀደለት::

*ዕዝራ* 7:10:: *ዕዝራ* የእግዚአብሔርን ሕግ በማጥናትና በማድረግ፣ ለእስራኤልም ሥርዐቱንና ሕጉን በማስተማር ራሱን ፈጽሞ ሰጥቶ ነበር::

**9. እግዚአብሔር በእምነት እርሱን መጠጊያቸው የሚያደርጉትን ሰዎች ይባርካል::**

ሩት:: *(መላው የሩት መጽሐፍ ይህንን በግሩም ሁኔታ ይገልጠዋል::)*

ሩት 2:12:: በዔዝም መልሶ፣ «. . . ስላደረግሽው ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋሽን ይክፈልሽ፤ በክንፉ ጥላ ሥር ለመጠለል የመጣሽበት የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ብድራትሽን አትረፍርፎ ይመልስልሽ::»

ሩት 2:20:: *(ሩት በቦዔዝ እርሻ ላይ ከቃረመች በኋላ ኑኃሚን አመሰገነችው::)* ኑኃሚንም ምራቷን፣ «በጎነቱን ለሕያዋንም ሆነ ለሙታን ማድረጉን ያልተወ እግዚአብሔር ይባርከው» አለቻት፤ ቀጥላም፣ «ሰውየው እኮ የሥጋ ዘመዳችን ነው፤ የመቤዠት ግዴታ ካለባቸው ዘመዶቻችን አንዱ እርሱ ነው» አለቻት::»



**10. ከእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ያልተፈጸመ አንድም ነገር የለም::**

ኢያሱ 23:14:: «እነሆ፤ አሁን የምድርን ሁሉ መንገድ ልሄድ ነው፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ መልካም ተስፋ ሁሉ አንዲቱን እንኳ እንዳላስቀረባችሁ፣ በፍጹም ልባችሁ በፍጹም ነፍሳችሁ ታውቃላችሁ፤ አንዱም ሳይቀር ሁሉም ተፈጽሞአል::»

**11. እግዚአብሔር በተጨማሪም ማስፈራራቱን ይቀጥላል::**

ኢያሱ 23:15-16:: ነገር ግን አምላካችሁ እግዚአብሔር የሰጣችሁ መልካሙ ተስፋ በሙሉ እንደ ተፈጸመ ሁሉ፣ እንደዚሁም አምላካችሁ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ከመልካሚቱ ምድር እስኪያጠፋችሁ ድረስ ክፉውን ነገር ያመጣባችኋል:: አምላካችሁ እግዚአብሔር ያዘዛችሁን ኪዳን ብታፈርሱ፣ ሄዳችሁም ሌሎችን አማልክት ብታገለግሉና ብትሰግዱላቸው የእግዚአብሔር ቁጣ በላያችሁ ይነዳል፤ ከሰጣችሁም ከመልካሚቱ ምድር በፍጥነት ትጠፋላችሁ::

**12. እግዚአብሔር የእስራኤልን ጠላቶች ለማሸነፍ የጌዴዎንን አነስተኛ ወታደሮች ተጠቀመ::**

መሳ. 7:1-25::

መሳ. 7:2-3:: እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፤ «ምድያማውያንን በእጃቸው አሳልፌ እንዳልሰጥ አብረውህ ያሉት ሰዎች በጣም ብዙ ናቸው፤ እስራኤላውያን የገዛ ኀይላቸው እንዳዳናቸው በመቍጠር እንዳይታበዩብኝ፣ <ማንም የፈራ ቢኖር የገለዓድን ተራራ ትቶ ወደ መጣበት ይመለስ?> ብለህ ለሕዝቡ ዐውጅ::» ስለዚህ ሃያ ሁለቱ ሺህ ሲመለሱ ዐሥሩ ሺህ ብቻ ቀሩ::

**13. እግዚአብሔር ከባድ ተልዕኮ ከሰጣቸው ሰዎች ጋር እንደሚሄድ ተስፋን ይሰጣል::**

ዘዳ. 31:7-8:: ከዚያም ሙሴ ኢያሱን ጠርቶ በእስራኤል ሁሉ ፊት እንዲህ አለው፤ «እግዚአብሔር (ያህዌ) ለአባቶቻቸው ሊሰጥ ወደ ማለላቸው ምድር ከዚህ ሕዝብ ጋር አብረህ ስለምትገባ፣

ምድሪቱን ርስታቸው አድርገህ ስለምታከፋፍል በርታ፤ ደፋርም ሁን። እግዚአብሔር (ያህዌ) ራሱ በፊትህ ይሄዳል፤ ከአንተም ጋር ይሆናል፤ ፈጽሞ አይለይህም፤ አይተውህምም፤ አትፍራ፤ ተስፋም አትቍረጥ።»

**14. ዮሴፍ ወደ ባርነት በመሸጡ የእግዚአብሔርን መጋቢነት አየ።**

ዘፍ. 45:1-14። *(ዮሴፍ ራሱን ለወንድሞቹ ገለጠላቸው።)*

ዘፍ. 45:4-8። ዮሴፍም ወንድሞቹን፣ «እስቲ ወደ እኔ ቀረብ በሉ» አላቸው፤ ወደ እርሱም በቀረቡ ጊዜ እንዲህ አለ፤ «ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ እኔ ዮሴፍ ነኝ፤ አሁንም በመሸጣችሁ አትቈጩ፣ በራሳችሁም ዐትዘኑ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሕይወት ለማዳን ሲል ከእናንተ አስቀድሞ እኔን ወደዚህ ልኮኛል። በምድር ላይ ራብ ከገባ ይኸው ሁለት ዓመት ሆነ፤ ከዚህ በኋላም የማይታረስባቸውና ሰብል የማይሰበሰብባቸው አምስት ዓመታት ገና አሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ሕይወታችሁን በታላቅ ማዳን ለመታደግና ዘራችሁ ከምድር ላይ እንዳይጠፋ በማሰብ ከእናንተ አስቀድሞ ወደዚህ ላከኝ። «ስለዚህ አሁን ወደዚህ የላከኝ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንጂ እናንተ አይደላችሁም፤ እርሱም ለፈርዖን እንደ አባት፣ በቤት ንብረቱ ላይ ጌታ፣ እንዲሁም በግብፅ ምድር ላይ ገዥ አደረገኝ።»

ዘፍ. 50:15-21 *(ዮሴፍ ለወንድሞቹ ይቅርታን እንዳደረገላቸው በድጋሚ አረጋገጠ።)*

ዘፍ. 50-19-21። ዮሴፍ ግን እንዲህ አላቸው፤ «አትፍሩ፤ እኔን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ቦታ ማን አስቀመጠኝ? እናንተ እኔን ለመጕዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚአብሔር(ኤሎሂም) ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው። አሁንም ቢሆን አትፍሩ፤ ለእናንተና ለልጆቻችሁ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ አደርግላችኋለሁ» በማለት አረጋግጦ፣ በደግ ቃል አናገራቸው።

**15. እግዚአብሔር አንዳንዴ ያሳዝናል፣ ሆኖም ግን እንደገና ምሕረት ያሳያል።**



ሰቆ. 3:31-33። እግዚአብሔር ሰውን፣ ለዘላለም አይጥልምና፤ መከራን ቢያመጣ እንኳ ይራራል፤ ታላቅ ፍቅሩ አይለወጥምና ሆን ብሎ ችግርን፣ ወይም መከራን በሰው ልጆች ላይ አያመጣምና።

**16. እግዚአብሔር መልካምና ክፉ ጊዜያትን ሁለቱንም ይናገራል፣ እንዲሁም ያመጣል።**

ሰቆ. 3:37-42። እግዚአብሔር ካላዘዘ በቀር፤ ተናግሮ መፈጸም የሚችል ማን ነው? ክፉም ሆነ መልካም ነገር፣ ከልዑል አፍ የሚወጣ አይደለምን? ታዲያ ሕያው ሰው በኀጢአቱ ሲቀጣ፣ ስለምን ያጕረመርማል? መንገዳችንን እንመርምር፤ እንፈትን፤ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ። ልባችንን ከእጃችን ጋር በሰማይ ወዳለው ወደ አምላካችን እንንሣ፤ እንዲህም እንበል፤ «ዐምፀናል፤ ኀጢአትም ሠርተናል፤ አንተም ይቅር አላልኸንም።»

**17. እረኛ ለበጐቹ እንደሚጠነቀቅ ሁሉ እንዲሁም እግዚአብሔር በታማኝነት ይጠነቀቅልናል።**

መዝ. 23።

**18. እግዚአብሔርን ደስ ስናሰኘው፣ ጠላቶቻችንም ከእኛ ጋር ሰላምን እንዲፈጥሩ ያደርጋል።**

ምሳ. 16:7። የሰው መንገድ እግዚአብሔርን ደስ ሲያሰኘው፤ ጠላቶቹ እንኳ አብረውት በሰላም እንዲኖሩ ያደርጋል።

**19. ሁሉም ገዢዎች በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ናቸው።**

ምሳ. 21:1። የንጉሥ ልብ በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ እርሱም እንደ ቦይ ውሃ ደስ ወዳሰኘው ይመራዋል።

**20. እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ምን ነገር ሊሆን እንዳለ አስቀድሞ ዐቅዷል፣ በተጨማሪም ዕቅዱን ይፈጽማል።**

ኢሳ. 46:10-13።

ኢሳ. 46:10። የመጨረሻውን ከመጀመሪያው፣ ገና የሚመጣውንም ከጥንቱ ተናግሬአለሁ፤ <ዐላማዬ የጸና ነው፤ ደስ የሚያሰኘኝንም ሁሉ አደርጋለሁ> እላለሁ።

21. ዝናብን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው:: በምትፈልጉበት ጊዜ ስለ ዝናብ ጸልዩ::

ዘካ. 10:1:: የበልግ ዝናብ እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁ፤ ማዕበሉን ደመና የሚያደርግ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ ለሰዎች በቂ ዝናብን፣ ለእንዳንዱም የምድርን ተክል ይሰጣል::

22. የዮናስ ታሪክ በአስደናቂ ሁኔታ የእግዚአብሔርን መጋቢነት ይገልጣል::

ዮናስ 1:4:: እግዚአብሔርም በባሕሩ ላይ ታላቅ ነፋስን ላከ፤ ከባድ ማዕበልም ተነሥቶ መርከቢቱን አንገላታት፤ ልትሰበርም ተቃረበች::

ዮናስ 1:17:: እግዚአብሔር ግን ዮናስን የሚውጥ ትልቅ ዓሣ አዘጋጀ፤ ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት አደረ::

ዮናስ 2:10:: እግዚአብሔርም ዓሣውን አዘዘው፤ ዮናስንም በደረቅ ምድር ላይ ተፋው::

ዮናስ 4:6-8:: እግዚአብሔር አምላክም የቅል ተክል አብቅሎ፣ የዮናስ ራስ ጥላ እንዲያገኝና ሙቀትም እንዳያስጨንቀው ከበላዩ እንዲያድግ አደረገ፤ ዮናስም ስለ ቅሉ እጅግ ደስ አለው:: ነገር ግን በሚቀጥለው ቀን በማለዳ እግዚአብሔር ትል አመጣ፤ ትሉም ቅሉን በላ፤ ቅሉም ደረቀ:: ፀሐይ ስትወጣ፣ እግዚአብሔር የሚያቃጥል የምሥራቅ ነፋስ አመጣ፤ ፀሐዩም የዮናስን ራስ አቃጠለ፤ እርሱም ተዝለፈለፈ፤ መሞትም ፈልጎ፣ «ከመኖር መሞት ይሻለኛል» አለ::

23. እግዚአብሔር፣ ኤርምያስ ከመወለዱ አስቀድሞ እንኳን ለነቢይነት መርጦት ነበር::

ኤር. 1:4-5:: የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ መጣ፤ እንዲህም አለኝ፤ «በማሕፀን ሳልሠራህ ዐወቅሁህ፤ ከመወለድህ በፊት ለየሁህ፤ ለሕዝቦችም ነቢይ እንድትሆን ሾምሁህ::»

24. እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ዕቅዶቹን፣ ፍጹም ፈቃዱን ይፈጽማል:: ማንም ሰው ሊያደናቅፈው ወይም ሊያቆመው



አይችልም::

ምሳ. 16:4:: እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለራሱ ዐላማ ሠርቶአል፤ ክፉዎችንም እንኳ ለጥፋት ቀን አዘጋጅቶአል::

ምሳ. 16:9:: ሰው በልቡ መንገዱን ያቅዳል፤ እግዚአብሔር ግን እርምጃውን ይወስንለታል::

ምሳ. 16:33:: ዕጣ በጉያ ውስጥ ይጣላል፤ ውሳኔው በሙሉ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው::

ምሳ. 21:30:: እግዚአብሔርን ለመቋቋም የሚያስችል፣ አንዳችም ጥበብ ማስተዋልና ዕቅድ የለም::

መዝ. 135:6:: በሰማይና በምድር፣ በባሕርና በጥልቅ ሁሉ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ደስ ያሰኘውን ሁሉ ያደርጋል::

25. እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ የጳውሎስን የሮም እስራት ወንጌልን ለማስፋፋት ተጠቀመበት::

ፊል. 1:12-14:: አሁንም ወንድሞች ሆይ፤ በእኔ ላይ የደረሰው ነገር ወንጌል በይበልጥ እንዲስፋፋ መርዳቱን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ:: ከዚህ የተነሣ እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንደ ሆነ፣ በቤተ መንግሥት ዘበኞችና በሌሎችም ሁሉ ዘንድ ታውቆአል:: በእኔ መታሰር ምክንያት በጌታ ካሉት ወንድሞች ብዙዎቹ የእግዚአብሔርን ቃል ያለ ፍርሃት፣ በድፍረት ለመናገር ብርታት አግኝተዋል::

26. እግዚአብሔር ዮሴፍን የግብፅ ንጉሥ እንዲሆን አዘጋጀው:: ይህ የእግዚአብሔር ድርጊት በልጆቹ የግል ሕይወት ጉዳዮች ላይ እግዚአብሔር ጣልቃ እንደሚገባ ያሳያል::

ሐዋ. 7:9-10:: የነገድ አባቶችም በዮሴፍ ቀንተው በባርነት ወደ ግብፅ ሸጡት፤ እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ስለ ነበር፣ ከመከራው ሁሉ አወጣው፤ በግብፅም ንጉሥ በፈርዖን ፊት ሞገስና ጥበብን አጐናጸፈው፤ ፈርዖንም በግብፅና በቤተ መንግሥቱ ሁሉ ላይ ኀላፊ አድርጎ ሾመው::

27. እግዚአብሔር፤ የእስራኤልን ልጆች መምራት ይችል ዘንድ

**ሙሴን በሕይወት ጠብቆ በግብጻውያን ጥበብ ሁሉ እንዲሠለጥን አደረገው፡፡**

ሐዋ. 7:20-22፡፡ «በዚህ ጊዜ ሙሴ ተወለደ፤ እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኘ ውብ ሕፃን ነበር፡፡ በአባቱም ቤት ሦስት ወር በእንክብካቤ አደገ፡፡ ወደ ውጭ በተጣለም ጊዜ የፈርዖን ልጅ አግኝታ ወሰደችው፤ እንደ ራሷ ልጅ አድርጋም አሳደገችው፡፡ ሙሴም የግብፆችን ጥበብ ሁሉ ተማረ፤ በንግግሩና በተግባሩም ብርቱ ሆነ፡፡»

**28. እግዚአብሔር፣ ዓላማውን ለመፈጸም ለዳንኤልና ለሦስት ጓደኞቹ ልዩ የሆነን የእውቀት ችሎታና ጥበብ ሰጣቸው፡፡ እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚያደርገውን እዩ፡፡**

ዳን. 1:17፡፡ እግዚአብሔር ለእነዚህ አራት ወጣቶች በማንኛውም ሥነ ጽሑፍና ትምህርት ዕውቀትና ማስተዋልን ሰጣቸው፤ ዳንኤልም ማንኛውንም ራእይና ሕልም የመረዳት ችሎታ ነበረው፡፡

ዳን. 6:3፡፡ ከመሳፍንቱና ከበላይ አስተዳዳሪዎቹ ሁሉ ይልቅ ዳንኤል ልዩ የጥበብ መንፈስ የሞላበት ሆኖ በመገኘቱ፣ ንጉሡ በመላው ግዛቱ ላይ ሊሾመው አሰበ፡፡

**29. እግዚአብሔር፣ ሕዝቡን ወደ ተስፋይቱ ምድር ይመልሳቸው ዘንድ አሳብን በክፉው ንጉሥ በቂሮስ ልብ ውስጥ አኖረ፡፡**

ዕዝራ 1:1፡፡ ቂሮስ የፋርስ ንጉሥ በሆነ በመጀመሪያው ዓመት፣ እግዚአብሔር የቂሮስን መንፈስ አነሣሥቶ በመንግሥቱ ሁሉ ዐዋጅ እንዲያስነግርና ይህም በጽሑፍ እንዲሰፍር አደረገ፤ ይህ የሆነው በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው፡፡

**30. የእግዚአብሔር እጅ በነህምያ ላይ ነበረ፣ ለዚህም ነው ንጉሥ አርጤክስስ ልመናውን የሰጠው፡፡**

ነህ. 2:4-9፡፡

ነህ. 2:8፡፡ «እንዲሁም ለንጉሡ ደን ጠባቂ ለአሳፍ፣ በቤተ መቅደሱ አጠገብ ላለው ግምብ በሮች፣ ለከተማዪቱ ቅጥርና እኔም



ለምገባበት ቤት ሠረገላ የሚሆን እንጨት እንዲሰጠኝ ደብዳቤ ይጻፍልኝ፤» መልካሚቱ የአምላኬ እጅ በእኔ ላይ ነበረችና ንጉሡም ፈቀደልኝ፡፡

# ንስሐ

በተጨማሪ እድገታዊ ቅድስናን በገጽ 170፤ ኀጢአትን ማሸነፍ በገጽ 142፤ እንዲሁም ማስጠንቀቂያዎችን በገጽ 232 ላይ ይመልከቱ።

1. ኢየሱስ ኀጢአተኞችን ወደ ንስሐ ይጠራል።

*ሉቃ. 5:27-32። (ፈሪሳውያን ኢየሱስን ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር በመብላቱ ተቃወሙ። ኢየሱስም ለምን ይህን እንዳደረገ አብራራ።)*

ሉቃ. 5:31-32። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም፤ እኔም ኀጢአተኞችን ወደ ንስሐ ልመልስ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም።»

2. ኢየሱስ በኀጢአታቸው የተቸገሩትን ወደ ደኅንነት ወደሚያደርስ ንስሐ ይጠራቸዋል።

ማቴ. 7:20-23። ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስ፣ «ንስሓ ግቡ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና» እያለ መስበክ ጀመረ።

3. ንስሐ ከልብ፣ እውነተኛም መሆን አለበት።

ማር. 7:20-23። ቀጥሎ እንዲህ አለ፤ «ከሰው የሚወጣ ያ ሰውን ያረክሰዋል፤ ከውስጥ፣ ከሰው ልብ የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፣ ሰው መግደል፣ ዝሙት፣ መስገብገብ፣ ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው። እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ ሰውንም ያረክሱታል።

ኤር. 4:3-4። እግዚአብሔር ለይሁዳና ለኢየሩሳሌም ሰዎች እንዲህ ይላል፤ «ዕዳሪውን መሬት ዕረሱ፤ በእሾህም መካከል አትዝሩ። እናንተ የይሁዳ ሰዎች፣ የኢየሩሳሌምም ነዋሪዎች፤ ለእግዚአብሔር ተገረዙ፤ የልባችሁንም ሸለፈት አስወግዱ፤ አለዚያ ስለ ሠራችሁት ክፋት፣ ቊጣዬ እንደ እሳት ይንበለበላል፤ ሊገታውም የሚችል የለም።»

ኢዩ. 2:12-13። «አሁንም ቢሆን፣ በጾም፣ በልቅሶና በሐዘን፣



በፍጹም ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ» ይላል እግዚአብሔር። ልባችሁን እንጂ፣ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፤ እርሱ መሓሪና ርኅሩኅ፣ ቊጣው የዘገየና ፍቅሩ የበዛ፣ ክፉ ነገር ከማምጣትም የሚታገሥ ነውና።

4. መንፈሳዊ ኀዘን ወደ ደኅንነት የሚመራውን ንስሐ ያመጣል።

*2ኛ ቆሮ. 7:8-11። (በፍቅር አነሣሽነት፣ ጳውሎስ የቆሮንቶስ አማኞችን ንስሐንና ደኅንነትን ወደሚያመጣው መንፈሳዊ ኀዘን መራቸው።)*

2ኛ ቆሮ. 7:10-11። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን ወደ ድነት ለሚያደርስ ንስሓ ያበቃል፤ ጸጸትም የለበትም። ዓለማዊ ሐዘን ግን ለሞት ያበቃል። ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው ሐዘን እንዴት ያለ ትጋት፣ እንዴት ያለ መልስ የመስጠት ችሎታ፣ እንዴት ያለ ቊጣ፣ እንዴት ያለ ፍርሀት፣ እንዴት ያለ ናፍቆት፣ እንዴት ያለ በጎ ቅናት፣ እንዴት ያለ ተግሣጽ እንዳስገኘላችሁ ተመልከቱ። በዚህም ጉዳይ ንጹሓን መሆናችሁን በሁሉ ረገድ አስመስክራችኋል።

5. ንስሐ በሚገባ አንድ ኀጢአተኛ ምክንያት በሰማይ ደስታ ይሆናል።

*ሉቃ. 15። (ኢየሱስ ይህን በጠፋው በግ፣ በጠፋው ድሪምና በጠፋው ልጅ ምሳሌዎች ላይ ተናገረ።)*

ሉቃ. 15:7። እላችኋለሁ፤ እንደዚሁም ንስሓ ከሚያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ፣ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።

6. እግዚአብሔር፣ ኀጢተኞች እንዲፈልጉትና ክፉ መንገዳቸውን እንዲተዉ ይጠራቸዋል፣ እንዲሁም ይቅር እንደሚላቸውም ቃል ይገባላቸዋል።

ኢሳ. 55:6-7። እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት። ክፉ ሰው መንገዱን፣ በደለኛም ሐሳቡን ይተው። ወደ እግዚአብሔር ይመለስ፤ እርሱም ምሕረት ያደርግለታል፤ ወደ አምላካችን ይመለስ፤ ይቅርታው ብዙ ነውና።

**7. እግዚአብሔር፣ ጣዖታትን በልባቸው ውስጥ ያኖሩትንና ክፋትን ተግባራዊ የሚያደርጉትን ሰዎች ለንስሐ ይጠራል።**

ሕዝ. 14:1-11።

ሕዝ. 14:6። «ስለዚህ ለእስራኤል ቤት እንዲህ በል፤ «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ «ንስሓ ግቡ! ከጣዖቶቻችሁ ተመለሱ፤ ጸያፍ ተግባራችሁንም ሁሉ ተዉ።»

**8. መንገድ የሳተ ኀጢአተኛ ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ፣ በሕይወት ይኖራል።**

ሕዝ. 18:21-22። «ኀጢአተኛ ከሠራው ኀጢአት ሁሉ ተመልሶ ሥርዐቴን ሁሉ ቢጠብቅ፣ ቀናና ትክክለኛውን ነገር ቢያደርግ ፈጽሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። በደሉ ሁሉ አይታሰብበትም፤ በጽድቅ መንገድ ሄዶአልና በሕይወት ይኖራል።»

**9. እግዚአብሔር በኀጢአተኛው ሞት አይደሰትም።**

ሕዝ. 18:23። በውኑ ኀጢአተኛ ሲሞት ደስ ይሰኛልን? ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ይልቁን ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ሲኖር ደስ አይለኝምን?

**10. እግዚአብሔር፣ ኀጢአተኞች ከክፉ መንገዳቸው በአፋጣኝ እንዲመለሱ ይጋብዛቸዋል።**

ሕዝ. 18:30-32። «የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ስለዚህ እንደየሥራችሁ በእያንዳንዳችሁ ላይ እፈርዳለሁ፤ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። እንግዲህ ንስሓ ግቡ! በኀጢአት እንዳትጠፉ፣ ከኀጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ። በእኔ ላይ የፈጸማችሁትን በደል ሁሉ ወደ ኋላ ጣሉት፤ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ ይኑራችሁ። የእስራኤል ቤት ሆይ፤ ለምን ትሞታላችሁ? ማንም እንዲሞት አልሻምና፣ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ወደ እኔ ተመለሱና በሕይወት ኑሩ!»

**11. ኢየሱስ ንስሐ ለመግባት ፈቃደኞች ባልሆኑት ሁሉ ላይ ፍርድን ያውጃል።**

ማቴ. 11:20-24። ከዚያም ኢየሱስ ብዙውን ታምራት



ያደረገባቸው ከተሞች ንስሓ ባለመግባታቸው እንዲህ ሲል ወቀሳቸው፤ «ወዮልሽ ኮራዚን፣ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ታምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ገና ድሮ ማቅ ለብሰው፣ ዐመድ ነስንሰው ንስሓ በገቡ ነበር። ስለዚህ እላችኋለሁ፤ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ቅጣቱ ይቀልላቸዋል። አንቺም ቅፍርናሆም ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ ማለት ፈለግሽ? ነገር ግን ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ታምራት በሰዶም ቢደረግ ኖሮ፣ እስከ ዛሬ በቆየች ነበር። ስለዚህ እልሻለሁ፤ በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ቅጣቱ ለሰዶም ይቀልላታል።

**12. ከቸርነቱ የተነሣ፣ እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን ወደ ንስሐ ይጠራል።**

ሮሜ 2:4። ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሓ የሚመራህ መሆኑን ሳትገነዘብ፣ የቸርነቱን፣ የቻይነቱን የትዕግሥቱን ባለጠግነት ትንቃለህ?

**13. በእልከኝነት ንስሐ ለመግባት ካልፈቀድህ፣ እግዚአብሔር ይቀጣሃል። ንስሓ ከገባህ ግን፣ ይቅር ይልሃል፣ ብሎም የዘለዓለም ሕይወትን ይሰጥሃል።**

ሮሜ 2:5-11።

ሮሜ 2:5-6። ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ ልብህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን በራስህ ላይ ቍጣን ታከማቻለህ። እግዚአብሔር «ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ይሰጠዋል»።

**14. ለእግዚአብሔር የንስሐ ጥሪ ትኩረት በማይሰጡ ሰዎች ላይ መቅሰፍት ይወርዳል።**

ምሳ. 1:24-33።

ምሳ. 1:24-28። ነገር ግን በተጣራሁ ጊዜ እምቢ ስላላችሁኝ፣ እጄንም ስዘረጋ ማንም ግድ ስላልነበረው፣ ምክሬን ሁሉ ስለ ናቃችሁ፣ ዘለፋዬንም ስላልተቀበላችሁ፣ እኔ ደግሞ በመከራችሁ እሥቅባችኋለሁ፤ መዓት በሚወርድባችሁም ጊዜ አፌዝባችኋለሁ፤

መዓት እንደ ማዕበል ሲያናውጣችሁ፣ መከራም እንደ ዐውሎ ነፋስ ሲጠራርጋችሁ፣ ሥቃይና ችግር ሲያጥለቀልቃችሁ አፌዝባችኋለሁ። «በዚያን ጊዜ ይጠሩኛል፤ እኔ ግን አልመልስላቸውም፤ አጥብቀው ይፈልጉኛል፤ ነገር ግን አያገኙኝም።»

**15. አመንዝራይቱ ሴት ንስሐ ገብታ ወደ ክርስቶስ ተመለሰች፤ ይቅርም ተባለች።**

ሉቃ. 7:36-50።

ሉቃ. 7:37-38። በዚያ ከተማ የምትኖር አንዲት ኀጢአተኛ ሴት፣ ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት በማእድ መቀመጡን በሰማች ጊዜ አንድ የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቶ ይዛ መጣች፤ ከበስተ ኋላው እግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች እግሩን በእንባዋ ታርስ፣ በራሷም ጠጕር ታብሰው ጀመር፤ እግሩንም እየሳመች ሽቱውን ቀባችው።

ሉቃ. 7:48-50። ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «ኀጢአትሽ ተሰርዮልሻል» አላት። አብረውት በማእድ ተቀምጠው የነበሩ እንግዶችም፣ «ይህ ኀጢአትን እንኳ የሚያስተሰርይ እርሱ ማን ነው?» ብለው በልባቸው አሰቡ። ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ» አላት።

**16. እግዚአብሔር ንስሐ ባልገቡት እስራኤላውያን ላይ ቁጣውን አወረደ።**

ኢሳ. 42:23-25። ከእናንተ ይህን የሚሰማ፣ ለሚመጣውም ጊዜ አስተውሎ የሚያደምጥ ማነው? ያዕቆብን ለዝርፊያ፣ እስራኤልን ለምርኮ የዳረገ ማነው? በኀጢአት የበደልነው፣ እግዚአብሔር አይደለምን? መንገዱን ለመከተል፣ ለሕጉም መታዘዝ አልፈለጉምና። ስለዚህ የሚነድ ቍጣውን፣ የጦርነትንም መዓት አፈሰሰባቸው፤ በእሳት ነበልባል ከበባቸው፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም፤ አቃጠላቸው፤ እነርሱ ግን ልብ አላሉም።

**17. ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፣ እርሱም ወደ እናንተ ይመለሳል።**

ሚል. 3:7። «ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከትእዛዛቴ ፈቀቅ ብላችኋል፤ አልጠበቃችኋቸውምም፤ ወደ እኔ ተመለሱ፤ እኔም ወደ



እናንተ እመለሳለሁ» ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት።

**18. በኀጢአታቸው ምክንያት የሚያለቅሱ ብፁዓን ናቸው።**

ማቴ. 5:4። የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፤ መጽናናትን ያገኛሉና።

**19. የእግዚአብሔር ሕዝብ ከክፉ መንገዳቸው ቢመለሱ፣ ይቅር ይላቸዋል።**

2ኛ ዜና 7:14። በስሜ የተጠራው ሕዝቤ ራሱን አዋርዶ ቢጸልይ፣ ፊቴን ቢፈልግና ከክፉ መንገዱ ቢመለስ፣ ከሰማይ እሰማዋለሁ፤ ኀጢአቱን ይቅር እላለሁ፤ ምድሩንም እፈውሳለሁ።

**20. ጳውሎስ ኀጢአተኞች ሁሉ ንስሐ መግባት፣ ወደ እግዚአብሔር መመለስና ንስሐቸውንም በሥራቸው ማሳየት እንዳለባቸው ሰበከ።**

ሐዋ. 26:19-20። «እንግዲህ፣ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፤ ከሰማይ ለታየኝ ራእይ አልታዘዝ አላልሁም፤ ነገር ግን በመጀመሪያ በደማስቆ ለሚኖሩ፣ ቀጥሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላሉት ሁሉ፣ ከዚያም ለአሕዛብ፣ ንስሓ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ፣ የንስሓም ፍሬ እንዲያሳዩ ገልጬ ተናገርሁ።»

# ደኅንነት

## (ሰውን ወደ ክርስቶስ መምራት)

**ከክርስቶስ ውጪ፣ እኛ ረዳት የለሾችና ኀጢአተኞ ነን።**

*እኛ ሁላችን ኀጢአተኞች ነን።*

**1. እኛ ሁላችን በኀጢአት ተወልደናል።**

*መዝ.* 51:5። ስወለድ ጀምሮ በደለኛ፣ ገና እናቴም ስትፀንሰኝ ኀጢአተኛ ነኝ።

**2. እኛ ሁላችን፣ እንደ በጐች ጠፍተናል።**

ኢሳ. 53:6። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ እያንዳንዳችንም በየመንገዳችን ነጐድን፤ እግዚአብሔርም፤ የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ ጫነው።

**3. ሁሉም በአዳም በኩል ኀጢአት ሠርቷል።**

ሮሜ 5:12። ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጢአት በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል።

ሮሜ 5:19። በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ፣ በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።

**4. አይሁዶችና አሕዛብ በአንድነት ኀጢአተኞች ናቸው።**

ሮሜ 3:9-12። እንግዲህ ምን እንላለን? እኛ ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ፣ ሁሉም ከኀጢአት በታች እንደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋል፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ «ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤ አስተዋይ የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም። ሁሉም ተሳስተዋል፤ በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ በጎ የሚያደርግም ማንም የለም፤ አንድም እንኳ።»

ሮሜ 3:22-24። ልዩነት የለም፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን



ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤»

**5. እኛ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲፈልጋቸው እንደ ወጣ ዓይነት የጠፉ በጐች ነን።**

ሉቃ. 15:3-7።

**6. እኛ ልክ እንደ ጠፋው ልጅ ነን።**

ሉቃ. 15:11-24።

**7. የጽድቅ ሥራችን እንኳ እንደ መርገም ጨርቅ ነው።**

ኢሳ. 64:6። ሁላችን እንደ ረከሰ ሰው ሆነናል፤ የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው፤ ሁላችን እንደ ቅጠል ረግፈናል፤ ኀጢአታችንም እንደ ነፋስ ጠራርጎናል።

**8. ኀጢአት የለብንም ብትሉ ራሳችሁን ታታልላላችሁ፣ እግዚአብሔርንም ውሸታም ታደርጉታላችሁ።**

1ኛ ዮሐ. 1:8-10። ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ ታማኝና ጻድቅ ነው፡ ኀጢአት አልሠራንም ብንል፣ እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።

**9. ከእግዚአብሔር ጸጋ ውጪ፣ ልቦቻችን አታላዮች፣ መንጻትም የማይችሉ ናቸው።**

ኤር. 17:9። የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነው፤ ፈውስም የለውም፤ ማንስ ሊረዳው ይችላል?

**10. በእግዚአብሔር ቅድስና ብርሃን ስናይ እኛ እጅግ ኀጢአተኞች ሰዎች ነን። በኢሳይያስ ሕይወትም የተከሰተው ይሄው ነው።**

ኢሳ. 6:1-5። ንጉሥ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን ከፍ ባለና በከበረ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፤ የልብሱም ዘርፍ ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፤ እያንዳንዳቸውም ስድስት ክንፍ ነበራቸው። በሁለት ክንፍ ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር፤ በሁለት ክንፍ እግራቸውን ይሸፍኑ ነበር፤

በሁለቱም ክንፍ ይበሩ ነበር፤ እርስ በርሳቸው በመቀባበልም «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፤ ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች» ይሉ ነበር። ከድምፃቸው ጩኸት የተነሣ የመድረኩ መሠረት ተናወጠ፤ ቤተ መቅደሱም በጢስ ተሞላ። እኔም፣ «ከንፈሮቹ የረከሱብኝ ሰው ነኝ፤ የምኖረውም ከንፈሮቹ በረከሱበት ሕዝብ መካከል ነው፤ ዐይኖቼም ንጉሡን፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን አይተዋልና ጠፍቻለሁ፣ ወዮልኝ!» አልሁ።

### እኛ በመንፈሳዊ እስራት ውስጥ እንገኛለን።

1. ከፍጥረታችን የኀጢአት እስረኞች ነበርን። ክርስቶስ ነፃ ያወጣናል።

ዮሐ. 8:31-36።

ዮሐ. 8:34-36። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፤ ኀጢአት የሚያደርግ የኀጢአት ባሪያ ነው፤ ባሪያ ለዘለቄታ በቤተ ሰቡ ውስጥ አይኖርም፤ ልጅ ግን ምን ጊዜም በቤት ይኖራል። እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ።

2. በኀጢአት መኖርን መቀጠል እስራት ነው።

2ኛ ጴጥ. 2:19። «እነርሱ ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው ሳሉ፣ ሌሎችን ነጻ ትወጣችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጧቸዋል፤ ሰው ለተገዛለት ለዚያ ነገር ባሪያ ነውና።»

3. ኢየሱስ ነጻ ያወጣናል።

ሮሜ 6:16-18። «ራሳችሁን እንደ ባሪያ አድርጋችሁ ስታቀርቡ ለምትታዘዙት ለእርሱ፣ ይኸውም ወደ ሞት ለሚወስደው ለኀጢአት ወይም ወደ ጽድቅ ለሚያደርሰው ለመታዘዝ ባሮች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ነገር ግን የኀጢአት ባሮች የነበራችሁ ቢሆንም፣ ለተሰጣችሁለት ትምህርት በሙሉ ልብ የታዘዛችሁ በመሆናችሁ፣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤ ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ፣ የጽድቅ ባሪያዎች ሆናችኋል።»

### እኛ ከእግዚአብሔር የተለየን ነን።

1. ከክርስቶስ ውጭ ከእግዚአብሔር ጋር ጠላቶች ነን።



ቈላ. 1:21-22። ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም ጠላቶች ነበራችሁ። አሁን ግን ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ሊያቀርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ፤

2. ከክርስቶስ ውጭ ተስፋ ቢሶች ነን።

ኤፌ. 2:12-13። በዚያን ዘመን ከክርስቶስ ተለይታችሁ፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቃችሁ፣ ለኪዳኑም ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ፣ በዓለም ላይ ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር እንደ ነበራችሁ አስታውሱ። አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባችኋል።

### የኀጢአት እውቀት በእግዚአብሔር ሕግ ይመጣል።

1. ሕጉን በማወቃችን ምክንያት ኀጢአትን እናውቃለን።

ሮሜ 3:20። ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ማንም በእርሱ ፊት ጻድቅ ነው ሊባል አይችልም፤ ይልቁንም በሕግ አማካይነት ኀጢአትን እንገነዘባለን።

2. ሕጉ ኀጢአትን እንድንረዳ ያደርገናል።

ሮሜ 7:7። እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ በራሱ ኀጢአት ነውን? በፍጹም አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ በኩል ባይሆን ኖሮ፣ ኀጢአት ምን እንደ ሆነ ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ «አትመኝ» ባይል ኖሮ፣ ምኞት ምን እንደ ሆነ በእርግጥ አላውቅም ነበር።

3. ኢየሱስ የራሱን የሕግ ማጠቃለያ ሰጠን።

ማቴ. 22:37-40። እርሱም እንዲህ አለው፤ «<ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤> ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው፤ ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም፣ <ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ> የሚለው ነው፤ ሕግና ነቢያት በሙሉ በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።»

4. እግዚአብሔር አሥርቱን ትእዛዛት ሰጥቶናል።

ዘፀ. 20:1-17።

## *እግዚአብሔር በራሱ ፍትሕ ኀጢአተኞችን ይቀጣል::*

1. እግዚአብሔር አስቀድሞ የራሱን ፍትሕ ለአዳም ገለጠ::

ዘፍ. 2:16-17:: እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰውን እንዲህ በማለት አዘዘው፤ «በአትክልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ትበላለህ:: ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ፤ ምክንያቱም ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ::»

2. የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነው::

ሮሜ 5:12:: ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጢአት በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል::

ሮሜ 6:23:: የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው::

3. ከፍጥረታችን እኛ ሁላችን ከእግዚአብሔር ርግማን በታች ነን::

ገላ. 3:10:: ሕግን በመጠበቅ የሚተማመኑ ሁሉ ከእርግማን በታች ናቸው፤ «በሕግ መጻሕፍት የተጻፈውን ሁሉ የማያደርግ የተረገመ ነው» ተብሎ ተጽፎአልና::

## *በየትኛውም መንገድ እኛ ራሳችንን ማዳን አንችልም::*

1. ከፍጥረታችን የእግዚአብሔር ጠላቶች ነን::

ሮሜ 8:7-8:: ለኀጢአት የተገዛ አእምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፤ መገዛትም አይችልም:: በሥጋ ፈቃድ የሚመሩትም እግዚአብሔርን ማስደሰት አይችሉም::

2. ከፍጥረታችን በኀጢአት ምክንያት የሞትንና የእግዚአብሔር ቁጣ ሰለባዎች ነበርን::

ኤፌ. 2:1-5:: እናንተ በበደላችሁና በኀጢአታችሁ ምክንያት ሙታን ነበራችሁ፤ በዚህም፣ የዓለምን ክፉ መንገድ ተከትላችሁ፣ በአየር ላይ ላሉት መንፈሳውያን ኀይላት ገዥ ለሆነውና አሁንም ለእግዚአብሔር በማይታዘዙት ሰዎች ላይ ለሚሠራው መንፈስ



እየታዘዛችሁ ትኖሩ ነበር:: እኛ ሁላችን በአንድ ወቅት የሥጋችንን ምኞት እያረካን፣ መንገዱንም እየተከተልን በመካከላቸው እንኖር ነበር፤ እንደ ሌሎቹም የቍጣ ልጆች ነበርን:: ነገር ግን በምሕረቱ ባለ ጠጋ የሆነ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ፣ በበደላችን ሙታን ሆነን ሳለ፣ በክርስቶስ ሕያዋን አደረገን፣ የዳናችሁት በጸጋ ነው::

3. እኛ የዳንነው በእምነትና በጸጋ አማካይነት ብቻ ነው::

ኤፌ. 2:8-9:: በእምነት፣ በጸጋ ድናችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ በሥራ አይደለም::

4. እግዚአብሔር የሚያድነን ዳግመኛ በመወለድና በመንፈስ ቅዱስ በኩል በሆነው መታደስ ነው::

ቲቶ 3:4-7:: ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ ስላደረግነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ አዳነን:: ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤ ይህንም መንፈስ እግዚአብሔር በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ አትረፍርፎ አፈሰሰው፤ ይኸውም በጸጋው ጸድቀን የዘላለምን ሕይወት ተስፋ ይዘን ወራሾች እንድንሆን ነው::

## ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋ፣ በእምነት አማካይነት ያድነናል::

### *ኢየሱስ ስለ ኀጢአተኞች ሲል ተሠቃየ እንዲሁም ሞተ፤ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ይድናሉ::*

1. ኢሳይያስ ስለ ያሕዌ መከራ ተቀባይ አገልጋይ ተነበየ::

ኢሳ. 53:1-11

ኢሳ. 53:4-6:: በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፤ ሕመማችንንም ተሸከመ፤ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፤ እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተሠቃየም ቈጠርነው:: ነገር ግን እርሱ ስለ መተላለፋችን ተወጋ፤ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን::

**2. ክርስቶስን በእምነት የሚቀበሉ ሁሉ ይድናሉ።**

ዮሐ. 1:12። ለተቀበሉትና በስሙ ላመኑት ሁሉ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን መብት ሰጣቸው።

**3. እንደ ተተነበየው፣ በእርሱ የሚያምኑ የዘላለምን ሕይወት ያገኙ ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ሰጠ።**

ዮሐ. 3:14-16። ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ፣ የሰው ልጅም እንዲሁ ሊሰቀል ይገባዋል፤ ይኸውም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው ነው። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና።»

**4. ኢየሱስ ለበጎቹ ሞተ።**

ዮሐ. 10:11፣ 14-15። «መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ መልካም እረኛ ሕይወቱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል፤ . . . መልካም እረኛ እኔ ነኝ፤ በጎቼን ዐውቃለሁ፤ እነርሱም ያውቁኛል፤ ይህም አብ እኔን እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው ነው። ሕይወቴንም ስለ በጎቹ አሳልፌ እሰጣለሁ።»

**5. በጎቹ የኢየሱስን ድምፅ ይሰማሉ፣ ይከተሉትማል፣ እንዲሁም የዘላለምን ሕይወት ያገኛሉ።**

ዮሐ. 10:27-28። «በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔ ዐውቃቸዋለሁ፤ እነርሱም ይከተሉኛል፤ እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ከቶ አይጠፉም፤ ከእጄም ሊነጥቃቸው የሚችል ማንም የለም።»

**6. እኛ በክርስቶስ ደም አማካይነት ተዋጅተናል።**

1ኛ ጴጥ. 1:18-19። ከቀድሞ አባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከንቱ ከሆነ ሕይወት የተዋጃችሁት በሚጠፋ ነገር፣ በብር ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እናንተ የተዋጃችሁት ነውርና እንከን እንደሌለበት በግ ደም፣ በክርስቶስ ክቡር ደም ነው።

**7. ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ወደደ፣ እንዲሁም ራሱን ስለ እርሷ አሳልፎ ሰጠ።**



ኤፌ. 5:25-27። ባሎች ሆይ፤ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳትና ራሱንም ስለ እርሷ አሳልፎ እንደ ሰጠ፣ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ በማንጻት እንድትቀደስ፣ እንዲሁም ጒድፍ ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዳች እንከን ሳይገኝባት ቅድስትና ነውር አልባ የሆነች ክብርት ቤተ ክርስቲያን አድርጎ ለራሱ ሊያቀርባት ነው።

**8. ኢየሱስ ብቸኛው መካከለኛ ነው።**

1ኛ ጢሞ. 2:5-6። አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤ ይህም በትክክለኛው ጊዜ ተመስክሮለታል።

**9. ክርስቶስ ለበርካታ ቸር ዓላማዎች ሲል ለማይገባቸው ኃጢአተኞች ሞተ።**

ሮሜ 5:8። ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያሳያል።

ፊል. 2:8። ሰው ሆኖ ተገልጦም፤ ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት፣ ያውም በመስቀል ላይ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ።

2ኛ ቆሮ. 5:21። እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኀጢአት አደረገው።

ዮሐ. 1:29። ዮሐንስ በማግሥቱ፣ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፤ «እነሆ! የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ በፊት ስለ ነበር ከእኔ ይልቃል» ያልሁት እርሱ ነው።

1ኛ ዮሐ. 4:9-10። እግዚአብሔር ፍቅሩን በመካከላችን የገለጠው እንዲህ ነው፤ እኛ በእርሱ አማካይነት በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ። ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስተሰርያ ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው።

ገላ. 3:13:: «በዕንጨት ላይ የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው» ተብሎ ስለ ተጻፈ፣ ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል::

1ኛ ጴጥ. 2:24:: ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በእርሱ ቍስል እናንተ ተፈውሳችኋል::

1ኛ ጴጥ. 3:18:: እንዲሁም ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ኀጢአት ሞቶአልና፤ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ፣ ጻድቅ የሆነው እርሱ ስለ ዐመፀኞች ሞተ፤ እርሱ በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ::

ዕብ. 9:14:: በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድናመልክ ኅሊናችንን ከምውት ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነጻ ይሆን!

10. በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናችን ምክንያት ይቅር ተብለናል፤ ጸድቀናል፣ ከበደለኝነት ስሜት ሁሉና ከኩነኔ ነጻ ሆነናል::

ሮሜ 3:21-24:: አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣ ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጦአል:: ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው:: ልዩነት የለም፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል::

ሮሜ 5:1:: «እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን::»

ሮሜ 8:1:: ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም::

ሮሜ 10:9-13:: «ኢየሱስ ጌታ ነው» ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ:: የምትጸድቀው በልብህ አምነህ ነው፤



የምትድነውም በአፍህ መስክረህ ነውና:: መጽሐፍ እንደሚለው፣ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም::» በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት የለም፤ አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፤ የሚለምኑትንም አብዝቶ ይባርካል፤ «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል::»

## በእምነት፣ በጸጋ በኩል የዳኑ ሰዎች ምሳሌዎች::

1. ቀረጥ ሰብሳቢው ሌዊ

*ሉቃ. 5:27-32::*

2. ቀረጥ ሰብሳቢው ዘኬዎስ::

*ሉቃ.* 19:9-10:: ኢየሱስም እንዲህ አለው፤ «ይህ ሰው ደግሞ የአብርሃም ልጅ ስለ ሆነ፣ ዛሬ መዳን ወደዚህ ቤት መጥቶአል፤ ምክንያቱም የሰው ልጅ የመጣው የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን ነው::»

3. በኢየሱስ እግር ላይ ያለቀሰችው የተጸጸተች ሴት::

*ሉቃ.* 7:48-50:: ኢየሱስም ሴቲቱን፣ «ኀጢአትሽ ተሰርዮልሻል. . . እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ» አላት::

4. የወጣላቸው ኀጢአተኞች በኢየሱስ ምሳሌዎች ላይ ተወክለዋል::

*ሉቃ.* 15:1-2:: አንድ ቀን፣ ቀረጥ ሰብሳቢዎችና «ኀጢአተኞች» ሁሉ ሊሰሙት በዙሪያው ተሰበሰቡ:: ፈሪሳውያንና ጸሐፍትም፣ «ይህ ሰው ኀጢአተኞችን ይቀበላል፤ ከእነርሱም ጋር ይበላል» እያሉ አጕረመረሙ::

*ሉቃ.* 15:3-7:: *(የጠፋው በግ ታሪክ::)*

*ሉቃ.* 15:8-10:: *(የጠፋው ድሪም [ሳንቲም] ታሪክ)*

*ሉቃ.* 15:11-31:: *(ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ታሪክ)*

5. በያዕቆብ የውሃ ጕድጓድ ስፍራ የነበረችው ሳምራዊት ሴት::

ዮሐ. 4:1-26::

6. በመስቀል ላይ የነበረው ነፍሰ ገዳይ::

ሉቃ. 23:39-43::

ሉቃ. 23:43:: ኢየሱስም፣ «እውነት እልሃለሁ፤ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» አለው::

7. በኋላ ታላቁ የወንጌል መልእክተኛ ጳውሎስ ወደ መሆን የመጣው የቤተ ክርስቲያን አሳዳጁ ሳውል::

*ሐዋ. 9:1-19:: (የጳውሎስ ለውጥ)*

1ኛ ጢሞ. 1:13-16:: ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ተሳዳቢ፣ አሳዳጅና ዐመፀኛ የነበርሁ ብሆንም፣ ባለማወቅና ባለማመን ስላደረግሁት ምሕረት ተደርጎልኛል፤ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆኑት እምነትና ፍቅር ጋርም የጌታችን ጸጋ ተትረፈረፈልኝ:: <ክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መጣ> የሚለው ቃል እውነተኛና ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ ነው፤ ከኀጢተኞችም ዋና እኔ ነኝ:: ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑና የዘላለምን ሕይወት ለሚቀበሉ ወሰን የሌለው ትዕግሥቱን ከኀጢአተኞች ዋና በሆንሁት በእኔ፣ እንደ ምሳሌ አድርጎ ያሳይ ዘንድ ምሕረትን አገኘሁ::

8. የፊልጵስዩስ የወኅኒ ጠባቂ::

ሐዋ. 16:25-26::

ሐዋ. 16:30-31:: ይዞአቸው ከወጣ በኋላ፣ «እናንት ሰዎች፤ እድን ዘንድ ምን ላድርግ?» አላቸው:: እነርሱም፣ «በጌታ በኢየሱስ እመን፤ አንተም ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ» አሉት::

እግዚአብሔር እንደ እኔና እንደ አንተ ያሉትን ኀጢአተኞች ይጠራል::

1. እግዚበአብሔር በመንፈስ የተራቡትንና የተጠሙትን ይጠራል::

ኢሳ. 55:1-3:: እናንት የተጠማችሁ ሁሉ ኑ፤ እናንት ገንዘብ የሌላችሁ፣ ወደ ውሆች ኑ፤ ኑና ግዙ፤ ብሉም፤ ኑና ያለ ገንዘብ፣ ያለ ዋጋ፣ የወይን ጠጅና ወተት ግዙ:: ገንዘባችሁን እንጀራ ባልሆነ ነገር ላይ ለምን ታጠፋላችሁ? በማያጠግብስ ነገር ላይ ለምን ጉልበታችሁን ትጨርሳላችሁ? ስሙ፤ እኔን ስሙኝ፤ መልካም



የሆነውንም ብሉ፤ ነፍሳችሁም በጥሩ ምግብ ትደሰታለች::

2. ኢየሱስ የሕይወት እንጀራና የሕይወት ውኃ ነው፤ ኀጢአተኞችም ወደ እርሱ እንዲመጡ ይጋብዛቸዋል::

ዮሐ. 6:35:: ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ በእኔም የሚያምን ፈጽሞ አይጠማም::»

ዮሐ. 7:37-38:: የበዓሉ መጨረሻ በሆነው በታላቁ ቀን፣ ኢየሱስ ቆሞ ከፍ ባለ ድምፅ እንዲህ አለ፤ «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን፣ መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል::»

ራእይ 22:17:: መንፈስና ሙሽራዪቱ፣ «ና» ይላሉ፤ የሚሰማም፣ «ና» ይበል፤ የተጠማም ሁሉ ይምጣ፤ የሚፈልግም ሁሉ የሕይወትን ውሃ በነጻ ይውሰድ::

3. ኢየሱስ ደካሞችንና ሸክም የከበደባቸውን ይጠራል::

ማቴ. 11:28-30:: «እናንተ ሸክም የከበዳችሁና የደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም ዕረፍት እሰጣችኋለሁ:: ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ በልቤ የዋህና ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና::»

4. እርሱ በጠባቡ ደጅ እንድንገባ ይጠራናል::

ማቴ. 7:13-14:: «በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤ ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ:: ወደ ሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው::»

5. እርሱ ንስሐ እንድንገባና በወንጌል እንድናምን ይጠራናል::

ማር. 1:14-15:: ዮሐንስ እስር ቤት ከገባ በኋላ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ወንጌል እየሰበከ ወደ ገሊላ ሄደ፣ «ጊዜው ደርሶአል፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፤ ንስሓ ግቡ፣ በወንጌልም እመኑ!» እያለ ይሰብክ ነበር::

6. እግዚአብሔርን በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት::

ኢሳ. 55:6-7:: እግዚአብሔር በሚገኝበት ጊዜ ፈልጉት፤ ቀርቦም ሳለ ጥሩት:: ክፉ ሰው መንገዱን፣ በደለኛም ሐሳቡን ይተው:: ወደ እግዚአብሔር ይመለስ፤ እርሱም ምሕረት ያደርግለታል፤ ወደ አምላካችን ይመለስ፤ ይቅርታው ብዙ ነውና::

7. ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ::

ዕብ. 3:7-19::

ዕብ. 3:7-9:: «ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፣ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣ በምድረ በዳ በፈተና ቀን፣ በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣ ልባችሁን አታደንድኑ:: አባቶቻችሁ በዚያ ተፈታተኑኝ፤ መረመሩኝ፣ ያደረግሁትንም ሁሉ ለአርባ ዓመት አዩ::»

8. እግዚአብሔር ኀጢአተኛውን ወደ ውጭ አያወጣውም::

ዮሐ. 6:37:: አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፤ ወደ እኔ የሚመጣውንም ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤

ሮሜ 10:13:: «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና::»

እኛ የዳንነው ጌታን በደስታ እንታዘዘውና እናገለግለው ዘንድ ነው::

1. ራሳችሁን ለእግዚአብሔር እንደ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ::

ሮሜ 12:1-2:: እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው:: መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ::

2. እኛ የዳንነው በወይኑ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ አማካይነት ብዙ ፍሬ እንድናፈራ ነው::



ዮሐ. 15:1-8::

ዮሐ. 15:8:: ብዙ ፍሬ በማፍራት ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን ብትገልጡ፣ በዚህ አባቴ ይከብራል::

3. እኛ የዳንነው ለኀጢአት እንድንሞት፣ ለእግዚአብሔር ሕያው እንድንሆን፣ እንዲሁም ለጽድቅ ባሮች እንድንሆን ነው::

ሮሜ 6:1-23::

4. እኛ የተጠራነው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት አዲስ ሕይወት እንድንኖር ነው::

ሮሜ 8:1-14::

ኤፌ. 5:1-21::

5. መንፈስ ቅዱስ ፍሬ እንድናፈራ ይረዳናል::

ገላ. 5:13-26::

6. ክርስቶስ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ እርሱ እንጂ ስለ ራሳችን እንዳንኖር ስለ እኛ ሞተ::

2ኛ ቆሮ. 5:15:: በሕይወት ያሉትም ለሞተላቸውና ከሙታን ለተነሣላቸው እንጂ ከእንግዲህ ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለ ሁሉ ሞተ::

በመዳናችን ምስጋና የማላበት ሕይወት ስለ መኖር የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎችን ለማግኘት እግዚአብሔርን መውደድን በገጽ 124፤ ሌሎችን መውደድና ማገልገልን በገጽ 118፣ መታዘዝን በገጽ 136፣ እንዲሁም እድገታዊ ቅድስናን በገጽ 170 ላይ ተመልከቱ::

# ግለኝነት

በተጨማሪ ሌሎችን መውደድንና ማገልገልን እንደ ግለኝነት ተቃራኒ አድርገህ በገጽ 118 ላይ ተመልከት።

1. ፍቅር የራሱን ፈላጊ አይደለም።

1ኛ ቆሮ. 13:5። «[ፍቅር] ተገቢ ያልሆነ ነገር አያደርግም፤ ራስ ወዳድ አይደለም፤ አይበሳጭም።»

2. ራስ ወዳድነት መራር ፍሬን ያመጣል።

ያዕ. 3:14-16። ነገር ግን መራራ ቅንአትና ራስ ወዳድነት በልባችሁ ቢኖር ኩራት አይሰማችሁ፤ እውነትንም አትካዱ። እንዲህ ያለችዋ ጥበብ ከላይ አይደለችም፤ ነገር ግን ከምድር ከሥጋና ከአጋንንት ናት። ቅናትና ራስ ወዳድነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሥራ ሁሉ ይገኛሉ።

3. ኢየሱስ ያዕቆብንና ዮሐንስን ስለ ራስ ወዳድ አስተሳሰባቸው ወቀሳቸው፣ እኛንም ወደ ትሕትና አገልግሎት ይጋብዘናል።

ማቴ. 20:20-28።

ማቴ. 20:26-28። በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም። ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤ የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን፤ የሰው ልጅ እንዲያገለግሉት ሳይሆን፣ ለማገልገልና ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ለመስጠት መጥቶአልና።

4. ኢየሱስ ራስን ወደ መካድ ይጠራናል።

ሉቃ. 9:23-25። ከዚያም ለሁሉም እንዲህ አላቸው፤ «በኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ምክንያቱም ነፍሱን ሊያድናት የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነፍሱን ስለ እኔ ብሎ የሚያጠፋት ግን ያድናታል። ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጠፋ ወይም ቢያጉድል ጥቅሙ ምንድን ነው?»

5. ራስ ወዳድ አትሁኑ፣ ነገር ግን ሌሎችንም አስቡ።



1ኛ ቆሮ. 10:24። እያንዳንዱ ሰው የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ የራሱን ብቻ አይፈልግ።

6. ሌሎችን እንዴት ማስደሰት እንደምትችሉ በማሰብ የኢየሱስን ምሳሌነት ተከተሉ።

ሮሜ. 15:2-3። እያንዳንዳችን ባልንጀራችንን ለማነጽ፣ እርሱንም ለመጥቀም ደስ የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል፤ ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር ግን፣ «አንተን የሰደቡበት ስድብ በእኔ ላይ ደረሰብኝ» ተብሎ እንተ ተጻፈው ሆነበት።

7. ስለ ራስህ ብቻ አታስብ። ኢየሱስን ምሰል፣ ስለ ሌሎች አስብ። ራስህን የምትሰጥ ሁን።

ፊል. 2:3-8።

ፊል. 2:3-5። ሌሎች ከእናንተ እንደሚሻሉ በትሕትና ቍጠሩ እንጂ፣ በራስ ወዳድነት ምኞት ወይም ከንቱ ውዳሴ ለማግኘት አንዳች አታድርጉ። እያንዳንዳችሁ ሌሎችን የሚጠቅመውን እንጂ፣ ራሳችሁን የሚጠቅመውን ብቻ አትመልከቱ። በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን።

# ራስን መግዛት፣ ራስን ማሠልጠን

1. ራስን አለመግዛት መከራን ያመጣል::

ምሳ. 25:28:: ራሱን የማይቈጣጠር ሰው፣ ቅጥሯ እንደ ፈረሰ ከተማ ነው::

2. ንዴቱን ሙሉ ለሙሉ የሚገልጥ ሰው እንደ ሞኝ ዓይነት ሥራ ይሠራል፤ ራሱን የሚገዛ ግን ጠቢብ ነው::

ምሳ. 29:11:: ተላላ ሰው ቍጣውን ያለ ገደብ ይለቀዋል፤ ጠቢብ ሰው ግን ራሱን ይቈጣጠራል::

3. ሁሉም ክርስቲያን ራሱን መግዛት ይችላል፤ ይህም የመንፈስ ፍሬ ነው::

ገላ. 5:22-23:: የመንፈስ ፍሬ ግን . . . ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው::

4. ራስን መግዛት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው::

2ኛ ጢሞ. 1:7:: እግዚአብሔር የኀይልና የፍቅር፣ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሀት መንፈስ አልሰጠንምና::

5. ራሳችንን እንድንገዛ ታዝዘናል::

1ኛ ጴጥ. 1:13:: ስለዚህ ልባችሁን አዘጋጁ፤ ራሳችሁንም ግዙ፤ ተስፋችሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ ለእናንተ በሚሰጠው ጸጋ ላይ ሙሉ በሙሉ አድርጉ::

6. አንድ ሰው ራሱን ሊገዛ ይችላል ይገባዋልም:: ለዚህም ብርቱ ጥረት ማድረግ አለበት::

2ኛ ጴጥ. 1:5-6:: በዚህም ምክንያት በሙሉ ትጋት በእምነታችሁ ላይ በጎነትን ለመጨመር ጣሩ፤ በበጎነት ላይ ዕውቀትን፣ በዕውቀት ላይ ራስን መግዛት፣ ራስን በመግዛት ላይ መጽናትን፣ በመጽናት ላይ እውነተኛ መንፈሳዊነትን፤ ...ጨምሩ::

7. ሽማግሌዎችም ሆኑ ወጣቶች ራስን መግዛትን መማር አለባቸው::

ቲቶ 2:2-6:: አረጋውያን ጭምቶች፣ የተከበሩ፣ ራሳቸውን የሚገዙና በእምነት፣ በፍቅርና በትዕግሥት ጤናማነት ያላቸው እንዲሆኑ ምከራቸው:: እንዲሁም አሮጊቶች በአኗኗራቸው የተከበሩ እንዲሆኑ፣ በጎ የሆነውን የሚያስተምሩ እንጂ የሰው ስም የሚያጠፉ ወይም በወይን ጠጅ ሱስ የተጠመዱ እንዳይሆኑ አስተምራቸው፤ እንዲህ ከሆኑ፣ ወጣት ሴቶች ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን እንዲወዱ ማስተማር ይችላሉ፤ የእግዚአብሔር ቃል በማንም ዘንድ እንዳይሰደብ ራሳቸውን የሚገዙና ንጹሓን፣ በቤት ውስጥ በሥራ የተጠመዱ፣ ቸሮች፣ ለባሎቻቸው የሚገዙ እንዲሆኑ ያስተምሯቸው:: እንዲሁም ወጣት ወንዶች ራሳቸውን እንዲገዙ ምከራቸው::

8. ለሁሉም ነገር ጊዜ አለው:: ራስን መግዛት ሁሉንም ነገር በራሱ ጊዜ ማድረግ ነው::

መክ. 3:1-8::

9. አስተሳሰባችንን ልንቆጣጠር እንችላለን::

2ኛ ቆሮ. 10:5:: በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን ክርክርና ከንቱ ሐሳብ ሁሉ እናፈርሳለን፤ አእምሮንም ሁሉ እየማረክን ለክርስቶስ እንዲታዘዝ እናደርጋለን::

10. ራስን መግዛት በብርሃን መመላለስ ነው::

1ኛ ተሰ. 5:4-8:: እናንተ ግን፣ ወንድሞች ሆይ፤ ይህ ቀን እንደ ሌባ ያስደነግጣችሁ ዘንድ በጨለማ ውስጥ አይደላችሁም፤ ሁላችሁም የብርሃን ልጆች፣ የቀንም ልጆች ናችሁና:: እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ ወገን አይደለንም፤ እንግዲህ እንንቃ፤ ራሳችንንም እንግዛ እንጂ እንደሚያንቀላፉት እንደ ሌሎቹ አንሁን:: የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉ፤ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና:: እኛ ግን የቀን ሰዎች ስለ ሆንን፣ እምነትንና ፍቅርን እንደ ጥሩር ለብሰን፣ የመዳንን ተስፋ እንደ ራስ ቍር ደፍተን ራሳችንን በመግዛት እንኑር::

11. በንግግራችሁ ራሳችሁን ግዙ፤ አንደበታችሁን ተቆጣጠሩ::

ምሳ. 20:19:: ሐሜተኛ ምስጢር ያባክናል፤ ስለዚህ ለፍላፊን

ሰው አርቀው::

በተጨማሪ በንግግር ጊዜ የበሰጠ ራስን ለመግዛት እንዲያስችላችሁ ተግባቦትን በገጽ 51 ላይ ተመልከቱ::

12. ራስን መግዛትን ተለማመዱ፣ እንዲሁም ለዓለማዊነት እምቢ በሉ::

ቲቶ 2:11-12:: ድነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር ጸጋ ለሰዎች ሁሉ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ በኀጢአት መኖርንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን፣ በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ፣ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንድንኖር ያስተምረናል::

13. በክርስቶስ የመቤዠት ፍቅር ተነቃቁ::

ቲቶ 2:13-14:: ይህም የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ በመጠባበቅ ነው፤ እርሱም ከክፋት ሊቤዠን መልካም የሆነውን ለማድረግ የሚተጋውን የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ለራሱ ያነጻ ዘንድ ራሱን ስለ እኛ ሰጥቷል::

14. ወዲያና ወዲህ አትበሉ፣ በቀላሉ በሌሎች አትውሰዱ::

1ኛ ቆሮ. 15:58:: ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ:: ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ::



# ለራስ መሳሳት፤ አዘኔታ

1. ኤልያስ ለጊዜው ለራሱ ሳስቶ ወደ ኮሬብ ኮበለለ::

1ኛ ነገ. 19::

1ኛ ነገ. 19:4-5:: በምድረ በዳም ውስጥ የአንድ ቀን መንገድ ተጓዘ፤ ወደ አንድ ክትክታ ዛፍ እንደ መጣም፣ ከሥሩ ተቀምጦ፣ ይሞት ዘንድ «እግዚአብሔር ሆይ፤ በቅቶኛል፣ እኔ ከቀደሙት አባቶቼ አልበልጥምና ነፍሴን ውሰዳት» ብሎ ጸለየ:: ከዚያም ከዛፍ ሥር ተጋደመ፤ እንቅልፍም ወሰደው::

2. እግዚአብሔር ኤልያስን አናገረው::

1ኛ ነገ. 19:9:: በዚያም ወደ አንዲት ዋሻ ገብቶ ዐደረ:: የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እርሱ መጣ፤ «ኤልያስ ሆይ፤ እዚህ ምን ታደርጋለህ? አለው::

3. የኤልያስን ማስተዛዘኛ ተመልከት::

1ኛነገ. 19:10:: እርሱም፣ «እኔ ለሰራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ፤ እስራኤላውያን ኪዳንህን ትተዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና:: የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ፤ አሁንም እኔን ለመግደል ይፈልጋሉ» አለ::

4. እግዚአብሔር የኤልያስን ችግር አቃለለ::

1ኛ ነገ. 19:11-18::

5. ዘማሪው አሳፍም ለራስ በመሳሳት ኀጢአት ውስጥ ለጊዜው ተዘፍቆ ነበር::

መዝ. 73::

6. የአሳፍን ማስተዛዘኛ (ስለ ራሱ ሳስቶ የተናገረውን) አዳምጡ::

መዝ. 73:13-14:: ለካ ልቤን ንጹሕ ያደረግሁት በከንቱ ነው፤ እጄንም በየዋህነት የታጠብሁት በከንቱ ኖሮአል! ቀኑን ሙሉ ተቀሠፍሁ፤ ጠዋት ጠዋትም ተቀጣሁ::

7. አሳፍ ለራሱ ከመሳሳት አገገመ::

መዝ. 73:15-28::

8. **እግዚአብሔር ለራስ ከመሳሳት የምንወጣበትን መንገድ ያመለክተናል::**

መዝ. 37::

9. **ለራስ ከመሳሳት ተመለሱ::**

ምሳ. 15:13:: ደስተኛ ልብ ፊትን ያፈካል፤ የልብ ሐዘን ግን መንፈስን ይሰብራል::

10. **ዮናስ ተቆጣ ለራሱም ሳሳ፣ ስለዚህም እግዚአብሔር ገሠጸው::**

ዮናስ 4:1-4::

ዮናስ 4:3-4:: አሁንም እግዚአብሔር ሆይ፤ ነፍሴን ውሰድ፤ ከመኖር መሞት ይሻለኛልና::



# የወሲብ ሕይወት

በተጨማሪ ማሕልየ መሓልይን ተመልከቱ::

1. **ወሲብ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው::**

ዕብ. 13:4:: ጋብቻ በሁሉም ዘንድ ይከበር፤ መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በአመንዝሮችና በሴሰኞች ሁሉ ላይ ይፈርዳል::

2. **ለትዳር ጓደኛችሁ የሚገባቸውን አድርጉ::**

1ኛ ቆሮ. 7:3:: ባል ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ ያድርግላት፤ ሚስትም እንዲሁ ለባሏ የሚገባውን ሁሉ ታድርግለት::

3. **አካላችሁ የትዳር ጓደኛችሁም አካል ነው::**

1ኛ ቆሮ. 7:4:: ሚስት አካሏ የራሷ ብቻ አይደለም፤ የባሏም ነው፤ እንዲሁም ባል አካሉ የራሱ ብቻ አይደለም፣ የሚስቱም ነው::

4. **መቆጠብ ያለባችሁ በጋራ ስምምነት ብቻ ነው፤ ምክንያቱም መቆጠብ ወደ ፈተና ይመራል::**

1ኛ ቆሮ. 7:5:: በጸሎት ላመትጋት ተስማምታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ካልሆነ በስተቀር፣ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ባለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ እንደ ገና አብራችሁ ሁኑ::

5. **በትዳር ጓደኞችሁ እርካታ አግኙ::**

ምሳ. 5:18-20:: ምንጭህ ቡሩክ ይሁን፤ በልጅነት ሚስትህም ደስ ይበልህ:: እርሷ እንደ ተወደደች ዋላ፣ እንደ ተዋበች ሚዳቋ ናት፤ ጡቶቿ ዘወትር ያርኩህ፤ ፍቅሯም ሁልጊዜ ይማርክህ:: ልጄ ሆይ፤ በአመንዝራ ሴት ፍቅር ለምን ትሰክራለህ? የሌላይቱንስ ሴት ብብት ስለ ምን ታቅፋለህ?

# ዘማዊነት

በተጨማሪ አመንዝራነትን በገጽ 11 ላይ፣ እንዲሁም ግብረ ሰዶማዊነትን በገጽ 109 ላይ ተመልከት::

1. ሴትን በፍትወት ምኞት ሆኖ መመልከት አመንዝራነት ነው::

ማቴ. 5:27-28:: <አታመንዝር> እንደ ተባለ ሰምታችኋል:: እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ሴትን በምኞት ዓይን የተመለከተ ሁሉ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሮአል::

2. ምናልባት ይህን ኢ-ግብረገባዊነት ለማስወገድ መንፈሳዊ ቀዶ ሕክምና ያስፈልግ ይሆናል::

ማቴ. 5:29-30:: ቀኝ ዓይንህ የኀጢአት ሰበብ ቢሆንብህ፣ አውጥተህ ወዲያ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል:: ቀኝ እጅህ የኀጢአት ሰበብ ቢሆንብህ ቈርጠህ ጣለው፤ ሰውነትህ በሙሉ ወደ ገሃነም ከሚጣል ከሰውነትህ አንዱን ክፍል ብታጣ ይሻልሃል::

3. ዝሙትን ግደሉ::

ቈላ. 3:5-7:: ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ፤ እነዚህም:- ዝሙት፣ ርኩሰት፣ ፍትወት፣ ክፉ ምኞትና አምልኮተ ጣዖት የሆነው መጐምጀት ናቸው:: በእነዚህም ምክንያት የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙት ላይ ይመጣል፤ እናንተም ቀድሞ በኖራችሁበት ሕይወት በእነዚህ ትመላለሱ ነበር::

4. የዝሙትን ኀጢአቶች ልታሸንፏቸው ትችላላችሁ::

ምሳ. 4:23:: ከሁሉም በላይ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት ምንጭ ነውና::

ምሳ. 4:24-27:: ጥመትን ከአፍህ አስወግድ፤ ብልሹ ንግግርም ከከንፈሮችህ ይራቅ:: ዐይኖችህ በቀጥታ ይመልከቱ፤ ትክ ብለህም ፊት ለፊት እይ:: የእግርህን ጐዳና አስተካክል፤ የጸናውን መንገድ ብቻ ያዝ:: ወደ ቀኝ ወደ ግራ አትበል፤ እግርህን ከክፉ ጠብቅ::

5. የዝሙት ኀጢአት ከልብ ይመነጫል::



ማቴ. 15:19-20:: ክፉ ሐሳብ፣ ነፍስ መግደል፣ ማመንዘር፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በሐሰት መመስከርና ስም ማጕደፍ ከልብ ይመነጫልና::

6. ዝሙት፣ ቅድመ-ጋብቻዊ ወሲብንም ጨምሮ በእግዚአብሔርና የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ በሆነው አካላችሁ ላይ ኀጢአት መሥራት እንደ ሆነ በጥልቀት ተገልጾአል::

1ኛ ቆሮ. 6:12-20::

7. ዘማዊዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም::

1ኛ ቆሮ. 6:9-10:: ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁምን? በዚህ ነገር አትታለሉ፤ ሴሰኞች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ አመንዝሮች፣ ወንደቃዎች፣ ግብረ ሰዶማውያን ወይም ሌቦች፣ ስግብግቦች፣ ሰካራሞች፣ ተሳዳቢዎችና ቀማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡

8. እግዚአብሔር ከዝሙት ኀጢአት ሊያነጻችሁ ይችላል::

1ኛ ቆሮ. 6:11:: ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ እንደዚህ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና፣ በአምላካችን መንፈስ ታጥባችኋል፤ ተቀድሳችኋል፣ ጸድቃችኋል::

9. ዝሙትን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ድል ልትነሡት ትችላላችሁ::

ገላ. 5:16-18:: እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙም:: ሥጋ መንፈስ የማይፈልገውን፣ መንፈስም ሥጋ የማይፈልገውን ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ፣ የምትፈልጉትን አታደርጉም:: በመንፈስ ብትመሩ ግን፣ ከሕግ በታች አይደላችሁም::

10. ሁሉም ኢ-ግብረገባዊነት ክልክል ነው:: እንደ ብርሐን ልጆች ተመላለሱ:: እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ::

ኤፌ. 5:3-17::

11. ኢየሱስ ነፃ ሊያወጣችሁ ይችላል::

ዮሐ. 8:31-36::

12. ለእግዚአብሔር ከመገዛታችሁ የተነሣ ራሳችሁን አንጹ::

2ኛ ቆሮ. 7:1:: እንግዲህ፣ ወዳጆች ሆይ፤ ይህ የተስፋ ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው::

13. ክርስቲያኖች ከእንግዲህ ወዲህ የሰውነት ክፍሎቻቸውን ኀጢአትን ለመፈጸም መጠቀም የለባቸውም:: መለወጥ ይችላሉ፤ ይገባቸዋል::

ሮሜ 6:15-23::

14. የሰዶምና የገሞራ ጥፋት ዘማዊ ሰዎችን ሁሉ ያስጠነቅቃል::

2ኛ ጴጥ. 2:4-10::

ይሁዳ 6-7:: የሥልጣን ስፍራቸውን ያልጠበቁትን ነገር ግን መኖሪያቸውን የተዉትን መላእክት በዘላለም እስራት እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ በጨለማ ጠብቆአቸዋል:: እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ፣ በዙሪያቸውም ያሉ ከተሞች ለሴሰኛነትና ከተፈጥሮ ሥርዐት ውጭ ለሆነ ሩካቤ ሥጋ ራሳቸውን አሳልፈው ሰጡ፤ እነርሱም በዘላለም እሳት በመቀጣት ለሚሠቃዩት ምሳሌ ሆነዋል::

15. እግዚአብሔር ሁላችንም ዝሙትን፣ ቅድመ-ጋብቻዊ ወሲብን ጨምሮ፣ እንድናስወግድ፣ እንዲሁም የገዛ ራሳችንን አካል መቆጣጠርን እንድንማር ይፈልጋል::

1ኛ ተሰ. 4:3-6:: የእግዚአብሔር ፈቃድ ከዝሙት ርቃችሁ እንድትቀደሱ ነው፤ ደግሞም እያንዳንዱ የገዛ ሰውነቱን በቅድስናና በክብር መያዝ እንዳለበት እንዲያውቅ ነው፤ ይህም እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ አሕዛብ በፍትወት ሥጋ ምኞት አይሁን:: በዚህም ነገር ማንም ተላልፎ ወንድሙን አያታል፤ ምክንያቱም ከዚህ በፊት እንደነገርናችሁና እንዳስጠነቀቅናችሁ ጌታ እንደ እነዚህ ያለውን ኀጢአት ሁሉ የሚፈጽሙትን ይበቀላል::



# ፈተና

በተጨማሪ ኀጢአትን ማሸነፍን በገጽ 142 ላይ እና እድገታዊ ቅድስናን በገጽ 170 ላይ ተመልከቱ::

1. ሰይጣን በተንኮል ሔዋንን ፈተናት::

ዘፍ. 3:1-4:: «እባብ እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ከፈጠራቸው የዱር እራዊት ሁሉ ተንኰለኛ ነበር፤ ሴቲቱንም፣ «በእርግጥ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) <በአትክልቱ ስፍራ ካሉ ዛፎች ከማናቸውም እንዳትበሉ> ብሎአልን? አላት:: ሴቲቱም እባቡን እንዲህ አለችው፤ «በአትክልቱ ስፍራ ካሉት ዛፎች ፍሬ መብላት እንችላለን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር (ኤሎሂም) <በአትክልቱ ስፍራ መካከል ከሚገኘው ዛፍ ፍሬ እንዳትበሉ፤ እንዳትነኩትም፤ አለበለዚያ ትሞታላችሁ> ብሎአል::» እባቡም ሴቲቱን እንዲህ አላት፤ «መሞት እንኳ አትሞቱም::»

2. ሰይጣን እስካሁንም የሚውጠውን እንደሚፈልግ አንበሳ ይዞራል::

1ኛ ጴጥ. 5:8-9:: ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል:: በዓለም ዙሪያ ያሉት ወንድሞቻችሁ ተመሳሳይ መከራ እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት::

3. አንዳንዴ ሰይጣን በብርሃን መልአክ ተመስሎ ይመጣል::

2ኛ ቆሮ. 11:14-15:: ይህም የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን ይለዋውጣል:: እንግዲህ የእርሱ አገልጋዮች፣ የጽድቅ አገልጋዮች ለመምሰል ራሳቸውን ቢለውጡ የሚያስገርም አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል::

4. አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን ሌሎች እንዲያደናቅፉን ይጠቀምባቸዋል::

ምሳ. 1:10:: ልጄ ሆይ፤ ኀጢአተኞች ቢያባብሉህ፣ እሺ አትበላቸው::

5. እግዚአብሔር ማንንም አይፈትንም:: እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ምኞት ተስቦ ሲጠላለፍ ነው::

*ያዕ. 1:13-15:: ማንም ሲፈተን፣ <እግዚአብሔር ፈተነኝ> አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ የሚፈተነው በራሱ ክፉ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ነው:: ምኞትም ከፀነሰች በኋላ ኀጢአትን ትወልዳለች፤ ኀጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች::*

6. ሰይጣንን ተቃወሙት::

*ያዕ. 4:7:: እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል::*

7. ኢየሱስ በሰይጣን ተፈትኖ ነበር::

*ማቴ. 4:1-11::*

8. ኢየሱስም በእያንዳንዱ ጊዜ ያሸነፈው የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም ነበር::

*ማቴ. 4:4፣ 7፣ 10:: (በእያንዳንዱ ጊዜ ኢየሱስ፣ «እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል» ይል ነበር::)*

9. ኢየሱስ ነቅተን እንድንጸልይ ይነግረናል፣ አለበለዚያ ለፈተና እንሸነፋለን::

*ማቴ. 6:13:: ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉው አድነን እንጂ::*

*ማቴ. 26:41:: ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነው::*

10. ሁሉም ክርስቲያን እንዳይወድቅ መጠንቀቅ አለበት::

*1ኛ ቆሮ. 10:12:: ስለዚህ ተደላድዬ ቆሜአለሁ የሚል ቢኖር እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ::*

11. የዲያብሎስን ሽንገላ ለመዋጋት የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ተላበሱ::

*ኤፌ. 6:10-18::*



*ኤፌ. 6:10-12:: በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ ጠንክሩ:: የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ መቋቋም ትችሉ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ:: ምክንያቱም ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኀይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ክርኩሳን መናፍስት ሠራዊት ጋር ነው::*

12. ዮሴፍ ኀጢአት እንዲሠራ በጲጢፋራ ሚስት ፈተና በቀረበለት ጊዜ እምቢ አለ::

ዘፍ. 39:6-20::

ዘፍ. 39:9-10:: «በዚህ ቤት ላይ ከእኔ የበለጠ ኀላፊነት ያለው ማንም የለም፤ እርሱ ያልሰጠኝ ነገር ቢኖር፣ አንቺን ብቻ ነው፤ ያውም ሚስቱ ስለሆንሽ ነው፤ ታዲያ፣ እኔ ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ እንዴት በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት ኀጢአት እሠራለሁ?»

# ልጆችን ማሠልጠን

በተጨማሪ ወጣትነትን በገጽ 245 ላይ ተመልከቱ::

1. **እግዚአብሔር ወላጆች ልጆቻቸውን እግዚአብሔርን ባማከለ መንገድ እንዲያሳድጓቸው ይፈልጋል:: ቀዳሚው ታሳቢ ግብ ልጆቻችሁ ጌታን ማወቃቸው፣ በእርሱ ማመናቸው፣ እርሱን መውደዳቸው፣ እርሱን መፍራታቸውና እርሱን ማገልገላቸው መሆን አለበት::**

   ዘዳ. 6:6-7:: ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዛት በልብህ ያዝ:: ለልጆችህም አስጠናቸው፤ በቤትህ ስተቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛና ስትነሣም ስለ እነርሱ ተናገር::

   ዮሐ. 17:3:: እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት::

   ኤፌ. 6:4:: አባቶች ሆይ፤ እናንተም ልጆቻችሁን አታስቈጧቸው፤ ነገር ግን በጌታ ምክርና ተግሣጽ አሳድጓቸው::

2. **ልጆችን የማሳደግ ቀዳሚ ኀላፊነት የአባት ነው::**

   ኤፌ. 6:4::

3. **ልክ እንደ ዘማሪው ዳዊት፣ ሁሉም ልጆች የተፀነሱትና የተወለዱት በኀጢአት ነው:: ወላጆች ወደሚያድነው የኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሊመሯቸው ይገባል::**

   መዝ. 51:5:: ስወለድ ጀምሮ በደለኛ፣ ገና እናቴም ስትፀንሰኝ ኀጢአተኛ ነኝ::

4. **ወላጆች የልጆችን ልብ ሊንከባከቡ ይገባል፣ ሥርዓት ማስያዝ ብቻ አይደለም ውጫዊውን ባሕርይ ለማስተካከል ተራ የሆነ ሙከራ ማድረግም አይደለም:: ማንኛውም ሰው ሲበድል በደሉ ከልቡ ይመነጫል::**

   ምሳ. 4:23:: ከሁሉም በላይ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት ምንጭ ነውና::»



   ማር. 7:21-23:: ከውስጥ፣ ከሰው ልብ የሚወጡት ክፉ ሐሳብ፣ ምንዝር፣ ስርቆት፤ ሰው መግደል፣ ዝሙት፣ መስገብገብ፣ ክፋት፣ ማታለል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስም ማጥፋት፣ ትዕቢት፣ ስንፍና ናቸው:: እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ ከሰው ይወጣሉ ሰውንም ያረክሱታል::

5. **አብዛኛዎቹ የልጅ ኀጢአተኛ ተፈጥሮዎች የሚነሡት ግለኛ ከሆነ ራስ ወዳድ አስተሳሰብ ነው::**

   በተጨማሪ ሌሎችን መውደድና ማገልገልን በገጽ 118 ላይ፣ እንዲሁም ግለኝነትን በገጽ 206 ላይ ተመልከቱ::

6. **ወላጆች ለልጆቻቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን ሊሰጧቸው ይገባል፣ እንዲሁ በዘፈቀደ ሕግጋትንና ደንቦችን ማስቀመጥ የለባቸውም::**

   ዘዳ. 6:6-7::

   ኤፌ. 6:4:: *(በገጽ 220 ላይ ቁጥር 1ን ተመልከት::)*

   ምሳ. 1:8-9:: ልጄ ሆይ፤ የአባትህን ምክር አድምጥ፤ የእናትህንም ትምህርት አትተው:: ለራስህ ሞገስን የሚያጐናጽፍ አክሊል፣ ዐንገትህን የሚያስውብ ድሪ ይሆንልሃል::

7. **መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት መንፈሳዊ እድገትን፣ በልጆችና በአዋቂዎች ዘንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሕይወት ለውጥን ያጎለብታል:: ኢየሱስ በሊቀ ካህናዊ ጸሎቱ ስለዚህ የጸጋ ሥራ ጸለየ::**

   ዮሐ. 17:17:: ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው::

8. **የአንተ አባታዊ ጥሪ እግዚአብሔር ለአማኞች ሁሉ አባት ለአብርሃም ከሰጠው ጥሪ ጋር ተመሳሳይ ነው::**

   ዘፍ. 18:19:: ትክክለኛና ቀና የሆነውን በማድረግ የእግዚአብሔርን (ያህዌ) መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤተ ሰቦቹን እንዲያዝ መርጬዋለሁ፤ ይኸውም እግዚአብሔር (ያህዌ) ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ሁሉ እንዲፈጸም ነው::

**9. ልጆቻቸው በእነርሱ አማካይነት ይመሩ ዘንድ እንዲሁም ይከተሏቸው ዘንድ ወላጆች መንፈሳዊ ምሳሌዎችን ማሳየት አለባቸው::**

ዘዳ. 6:4-6:: እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አንድ እግዚአብሔር (ያህዌ) ነው:: አምላክህን እግዚአብሔርን (ያህዌ ኤሎሂም) በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይልህ ውደድ:: ዛሬ የምሰጥህን እነዚህን ትእዛዛት በልብህ ያዝ::

**10. አባት የገዛ ራሱን ቤተሰብ ማስተዳደርና ልጆቹ ተገቢውን አክብሮት እየሰጡት መታዘዛቸውን መከታተል አለበት::**

1ኛ ጢሞ. 3:4:: ልጆቹን ታዛዥና አክባሪ አድርጎ በማሳደግ የገዛ ቤተ ሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳድር ሊሆን ይገባል::

**11. ፍትሕ አልባ የሆኑ ነገሮችን እንዲያከናውኑ በመጠበቅ ወይም ባለ መገሠጽ ልጆቻችሁን አታስቆጡአቸው::**

ኤፌ. 6:4:: *(በገጽ 220 ላይ ቁጥር «1» ን ተመልከት::)*

ቈላ. 3:21:: አባቶች ሆይ፤ ተስፋ እንዳይቈርጡ ልጆቻችሁን አታስመርሯቸው::

**12. ፍቅር እውነተኛ የሆነን ተግሣጽ ይጠይቃል::**

ምሳ. 13:24:: በአርጩሜ ከመቅጣት የሚሳሳለት ልጁን ይጠላል፤ የሚወደው ግን በጥንቃቄ ይቀጣዋል::

ምሳ. 22:15:: ሞኝነት በሕፃን ልብ ታስሮአል፤ የተግሣጽ በትር ግን ከእርሱ ያርቅለታል::

ምሳ. 23:13-14:: ልጅን ከመቅጣት ወደ ኋላ አትበል፤ በአርጩሜ ብትገርፈው አይሞትም:: በአርጩሜ ቅጣው፤ ነፍሱንም ከሞት አድናት::

ምሳ. 29:15:: የተግሣጽ በትር ጥበብን ታጐናጽፋለች፤ መረን የተለቀቀ ልጅ ግን እናቱን ያሳፍራል::

ምሳ. 29:17:: ልጅህን ቅጣው፤ ሰላም ይሰጥሃል፤ ነፍስህንም ደስ ያሰኛታል::

**13. የእግዚአብሔርን ምሳሌነት ተከተል፣ ምክንያቱም እርሱ**



**ልጆቹን ለጥቅማቸው ሲል በፍቅር ይቀጣቸዋል::**

ዕብ. 12:5-11::

**14. እርሱ ለልጆቹ በፍቅር ይነሣሣል::**

ዕብ. 12:6:: ምክንያቱም ጌታ የሚወደውን ይገሥጻል፤ እንደ ልጅ የሚቀበለውንም ይቀጣል::

**15. እግዚአብሔር ቅጣት እንዲያም አድርጎ ዐቅዶታል:: እርሱ ሁልጊዜ ብዙ ፍሬን በውስጣችን ያስከትል ዘንድ ለጥቅማችን ይቀጣናል::**

ዕብ. 12:11:: ቅጣት ሁሉ በወቅቱ የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፤ በኋላ ግን ለሰመዱት ሰዎች የጽድቅና የሰላም ፍሬ ያስገኝላቸዋል::

**16. ዔሊ ልጆቹን ያሞላቀቀ ወላጅ ስለነበረ እግዚአብሔር ፈረደበት::**

1ኛ ሳሙ. 3:1-18::

1ኛ ሳሙ. 3:13:: ዔሊ በሚያውቀስ ኀጢአት ምክንያት በቤተ ሰቡ ላይ ለዘላለም እንደምፈርድ ነግሬው ነበር፤ ልጆቹ አስጸያፊ ነገር አድርገዋል፤ እርሱ ግን አልከለከላቸውም::

**17. ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው::**

ምሳ. 22:6:: ልጅን የሚሄድበትን መንገድ አስተምረው፤ በሚሸመግልበት ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ አይልም::

**18. እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ...**

መዝ. 127:1-2:: እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፣ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፣ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል:: የዕለት ጒርስ ለማግኘት በመጣር፣ ማልዳችሁ መነሣታችሁ፣ አምሽታችሁም መተኛታችሁ ከንቱ ነው፤ እርሱ ለሚወዳቸው እንቅልፍን ያድላልና::

**19. ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው::**

መዝ. 127:3:: እነሆ፣ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፤ የማሕፀንም ፍሬ ከቸርነቱ የሚገኝ ነው::

# መታመን፣ እግዚአብሔርን ማመን

በተጨማሪ መጽናናትን በገጽ 46፣ ፍርሃትን በገጽ 88 ላይ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን መጋቢነት በገጽ 176 ላይ ተመልከቱ።

1. በጌታ መታመን።

*ምሳ. 3:5-6።* በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤ እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል።

2. ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም።

*ኤር. 32:17፣ 26-27።* «አቤት፣ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰማያትንና ምድርን በታላቅ ኀይልህና በተዘረጋች ክንድህ ፈጥረሃል፤ የሚሳንህም አንዳች ነገር የለም።» ከዚያም በኋላ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ እንዲህ ሲል መጣ፤ «እነሆ፣ እኔ የሰው ልጆች ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ፤ በውኑ የሚያቅተኝ ነገር አለን?»

3. የእግዚአብሔርን ክብርና ኀይል ተመልከቱ።

1ኛ ዜና 29:10-13።

1ኛ ዜና 29:11-12። እግዚአብሔር ሆይ፣ በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የአንተ ነውና፤ ታላቅነት፣ ኀይል፣ ክብርና ግርማ የአንተ ነው። እግዚአብሔር ሆይ፤ መንግሥትም የአንተ ነው፤ አንተም እንደ ራስ ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያልህ ነህ። ባለጠግነትና ክብር የሚገኘው ከአንተ ነው፤ አንተም የሁሉ ገዥ ነህ፤ ከፍ ከፍ ለማድረግ፣ ለሁሉም ብርታትን ለመስጠት፣ ብርታትና ኀይል በእጅህ ነው።

4. እግዚአብሔር እረኛህ ነው።

*መዝ. 23።*

5. እግዚአብሔር የአማኝ ብርሃንና ደኅንነት ነው።

*መዝ. 27።* (መዝሙሩን በአጠቃላይ ተመልከቱ፤ በተለይም ለቁጥር 1፣ 2፣ 5፣ 7፣ 8፣ 13፣ 14 ትኩረት ስጡ።)

*መዝ. 27:8።* «ፊቴን ፈልጉ» ባልህ ጊዜ፤ ልቤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ፊትህን እሻለሁ አለች።



*መዝ. 27:13-14።* የእግዚአብሔርን ቸርነት፣ በሕያዋን ምድር እንደማይ፣ ሙሉ እምነቴ ነው። እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤ አይዞህ፣ በርታ፣ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።

6. እግዚአብሔር የአማኝ መጠጊያና ኀይል ነው።

*መዝ. 91:1-2።* በልዑል መጠጊያ የሚኖር፣ ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ሥር ያድራል። እግዚአብሔርን፣ «መጠጊያዬ፣ ምሽጌ፣ የምታመንብህ አምላኬ» እለዋለሁ።

7. ዓይኖቻችሁን ወደ ተራራ አንሡ።

*መዝ. 121።* (እግዚአብሔር ረዳታችን፣ ተቆጣጣሪያችንና ጠባቂያችን እንደ ሆነ የሚናገረውን መዝሙር በአጠቃላይ ተመልከቱ።)

8. ኢየሱስ ማዕበሉን ጸጥ አሰኝና ደቀ መዛሙርቱን ስለ እምነት ጕዶሎነታቸው ወቀሳቸው።

*ማቴ. 8:23-27።*

9. ኢየሱስ ጴጥሮስን ስለ እምነቱ ጕዶሎነት ወቀሰው?

*ማቴ. 14:22-31።* (ኢየሱስ በውኃው ላይ ተራመደ፤ ጴጥሮስ ሞከረና ወደቀ።)

*ማቴ. 14:31።* ኢየሱስም ወዲያውኑ እጁን ዘርግቶ ያዘውና፣ «አንተ እምነት የጐደለህ፤ ለምን ተጠራጠርህ?» አለው።

10. እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ምሕረቱም በየማለዳው አዲስ ነው።

*ሰቆ. 3:22-24።* ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና። ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው፤ ታማኝነትህም ብዙ ነው።

11. እግዚአብሔር ሁልጊዜ ታማኝ ነው።

*ሰቆ. 3:32።* መከራን ቢያመጣ እንኳ ይራራል፤ ታላቅ ፍቅሩ አይለወጥምና።

12. በእግዚአብሔር ተማመን፣ ደስም ይበልህ፤ እርሱንም በትዕግሥት ተጠባበቀው።

መዝ. 37:1-7።

መዝ. 37:3። በእግዚአብሔር ታመን፣ መልካምንም አድርግ፤ በምድሪቱ ተቀመጥ፤ ዘና ብለህ ተሰማራ።

መዝ. 37:4። በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፤ የልብህንም መሻት ይሰጥሃል።»

መዝ. 37:5-6። መንገድህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ፤ በእርሱ ታመን፤ እርሱም ያከናውንልሃል፤ ጽድቅህን እንደ ብርሃን፣ ያንተን ፍትሕ እንደ ቀትር ፀሓይ ያበራዋል።

መዝ. 37:7። በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል፤ በትዕግሥትም ተጠባበቀው።

13. ለምን ትቆዝማላችሁ? በእግዚአብሔር ተስፋ አድርጉ።

መዝ. 42።

መዝ. 42:5። ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ? ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ? ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤ አዳኜና አምላኬን፣ ገና አመሰግነዋለሁና።

14. እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኀይላችን ነው።

መዝ. 46።

15. እግዚአብሔር በቅርበት ያውቀናል፤ እርሱ ሁልጊዜ ይመራናል።

መዝ. 139:1-11።

መዝ. 139:1-3። እግዚአብሔር ሆይ፤ መረመርኸኝ፤ ደግሞም ዐወቅኸኝ። አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ታውቃለህ፤ የልቤንም ሐሳብ ገና ከሩቁ ታስተውላለህ። መሄድ መተኛቴን አጥርተህ ታውቃለህ፤

መዝ. 139:9-10። በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር፣ እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣ በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች።

16. እግዚአብሔር ይሸከመናል፤ ይመራናልም።



መዝ. 73:23-24። ይህም ሆኖ ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ፤ አንተም ቀኝ እጄን ይዘኸኛል። በምክርህ መራኸኝ፤ ኋላም ወደ ክብር ታስገባኛለህ።

17. ወደ መጠጊያችሁ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ።

መዝ. 73:28። ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል፤ ጌታ እግዚአብሔርን መጠጊያዬ አድርጌዋለሁ፤ ስለ ሥራህም ሁሉ እናገር ዘንድ።

18. እግዚአብሔር ሕዝቡን ያጽናናል፣ መታመናቸውንም በእርሱ ላይ እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል።

ኢሳ. 40።

ኢሳ. 40:11። መንጋውን እንደ እረኛ ያሰማራል፤ ጠቦቶቹን በክንዱ ይሰበስባል፤ በዕቅፉም ይይዛቸዋል፤ የሚያጠቡትንም በጥንቃቄ ይመራል።

ኢሳ. 40:28-31። አታውቅምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፣ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው። አይደክምም፣ አይታክትም፤ ማስተዋሉም በማንም አይመረመርም። ለደከመው ብርታት ይሰጣል፤ ለዛለው ጉልበት ይጨምራል። ወጣቶች እንኳ ይደክማሉ፤ ይታክታሉም፤ ጕበዛዝትም ተሰናክለው ይወድቃሉ። እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን፣ ኀይላቸውን ያድሳሉ፤ እንደ ንስር በክንፍ ይወጣሉ፤ ይሮጣሉ፤ አይታክቱም፤ ይሄዳሉ፤ አይደክሙም።

19. አትፍሩ፤ እናንተ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ።

ኢሳ. 43:1-3። አሁን ግን፣ ያዕቆብ ሆይ! የፈጠረህ፤ እስራኤል ሆይ! የሠራህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ «ተቤዥቼሃለሁና አትፍራ፤ በስምህ ጠርቼሃለሁ፤ አንተ የእኔ ነህ፤ በውሃ ውስጥ በምታልፍበት ጊዜ፣ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ ወንዙን ስትሻገረው፣ አያሰጥምህም፤ በእሳት ውስጥ ስትሄድ፣ አያቃጥልህም፤ ነበልባሉም አይፈጅህም። እኔ እግዚአብሔር አምላክህ፣ የእስራኤልም ቅዱስ መድኀኒትህ ነኝና።

**20. አትፍሩ፤ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው::**

ኢሳ. 41:10:: እኔ ከአንተ ጋር ነኝና አትፍራ፤ አምላክህ ነኝና አትደንግጥ:: አበረታሃለሁ፤ እረዳሃለሁ፤ በጽድቄም ቀኝ ደግፌ እይዝሃለሁ::

**21. በመከራችሁ ቀን እግዚአብሔርን ጥሩ::**

መዝ. 50:15:: በመከራ ቀን ጥራኝ፤ አድንሃለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ::

**22. እግዚአብሔርን መጠጊያችሁ አድርጉት::**

መዝ. 57:1:: ማረኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ማረኝ፤ ነፍሴ አንተን መጠጊያ አድርጋለችና፤ በክንፎችህ ሥር እጠለላለሁ::

**23. የሰማዩ አባታችሁ ይንከባከባችሁ ዘንድ ታመኑት:: እግዚአብሔር ለወፎችና ለአበቦች እንኳ እንዴት እንደሚጠነቀቅላቸው አስቡ:: እናንተ ከእነርሱ ይልቅ ዋጋ ያላችሁ ናችሁ::**

ማቴ. 6:25-34::

**24. የእግዚአብሔር አገልጋይ ኢያሱ ታላቅ ሥራ ተሰጥቶታል:: ጌታም እንዲበረታና ደፋር እንዲሆን ይመክረዋል::**

ኢያሱ 1:1-9::

ኢያሱ 1:9:: በምትሄድበት ሁሉ እግዚአብሔር አምላክህ ከአንተ ጋር ነውና አይዞህ፤ በርታ፤ ጽና፤ አትፍራ፤ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?

**25. በጌታ መታመን የልብ ሰላምን ያመጣል:: በማይለወጠው ፍቅሩ ላይ ታመን::**

ኢሳ. 26:3-4:: በአንተ ላይ ታምናለችና፣ በአንተ የምትደገፈውን ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ::

መዝ. 9:9:: እግዚአብሔር ለተጨቈኑት ዐምባ ነው፤ በመከራም ጊዜ መጠጊያ ይሆናቸዋል::

መዝ. 28:7-8:: እግዚአብሔር ብርታቴና ጋሻዬ ነው፤ ልቤ



በእርሱ ይታመናል፤ እርሱም አግዞኛል፤ ልቤ ሐሤት አደረገ፤ በዝማሬም አመሰግነዋለሁ:: እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብርታታቸው ነው፤ ለቀባውም የመዳን አምባ ነው::

መዝ. 33:18-22: እነሆ፤ የእግዚአብሔር ዐይኖች በሚፈሩት ላይ ናቸው፤ ምሕረቱንም በሚጠባበቁት ላይ አትኩረዋል:: በዚህም ነፍሳቸውን ከሞት ያድናል፤ በራብ ዘመንም በሕይወት ያኖራቸዋል:: ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ ታደርጋለች፤ እርሱ ረዳታችንና መጠጊያችን ነው::

መዝ. 36:5-9:: እግዚአብሔር ሆይ፣ ምሕረትህ እስከ ሰማያት ይደርሳል፤ ታማኝነትህም እስከ ጠፈር ይመጥቃል:: ጽድቅህ እንደ ታላላቅ ተራሮች፣ ፍርድህም እጅግ ጥልቅ ነው፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሰውንም እንስሳንም ታድናለህ:: አምላክ ሆይ፣ ምሕረትህ እንዴት ክቡር ነው! የሰዎች ልጆች ሁሉ፣ በክንፎችህ ጥላ ሥር መጠጊያ ያገኛሉ:: ከቤትህ ሲሳይ ይመገባሉ፤ ከበረከትህም ወንዝ ይጠጣሉ:: የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና፤ በብርሃንህም ብርሃንን እናያለን::

**26. እግዚአብሔር የሚታመኑበትን ይንከባከባል::**

ናሆም 1:7:: እግዚአብሔር መልካም ነው፤ በጭንቅ ጊዜም መሸሸጊያ ነው:: ለሚታመኑበት ይጠነቀቅላቸዋል::

**27. በዓለማዊ ኀይል ወይም በክፉዎች ሰዎች አትታመን::**

ኢሳ. 31:1:: ወደ እስራኤል ቅዱስ ለማይመለከቱ፣ ከእግዚአብሔርም ርዳታን ለማይሹ፣ ነገር ግን፣ ለርዳታ ብለው ወደ ግብፅ ለሚወርዱ፣ በፈረሶች ለሚታመኑ፣ በሠረገሎቻቸው ብዛት፣ በፈረሶቻቸውም ታላቅ ብርታት ለሚመኩ ወዮላቸው!

ኤር. 17:7-8:: «ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን፣ መታመኛውም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው:: በውሃ ዳር እንደ ተተከለ፣ ሥሩንም ወደ ወንዝ እንደ ሰደደ ዛፍ ነው፣ ሙቀት ሲመጣ አይፈራም፤ ቅጠሉም ዘወትር እንደ ለመለመ ነው፤ በድርቅ ዘመን አይሠጋም፤ ፍሬ ማፍራቱንም አያቋርጥም::

**28. እግዚአብሔር ሊረሳን አይችልም።**

ኢሳ. 49:14-16። ጽዮን ግን፣ «እግዚአብሔር ትቶኛል፤ ጌታም ረስቶኛል» አለች። «እናት የምታጠባውን ልጇን ልትረሳ ትችላለችን? ለወለደችውስ ልጅ አትራራለትምን? ምናልባት እርሷ ትረሳ ይሆናል፣ እኔ ግን አልረሳሽም። እነሆ፣ በእጄ መዳፍ ላይ ቀርጬሻለሁ፤ ቅጥሮችሽ ምንጊዜም በፊቴ ናቸው።»

**29. በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እረፉ። ሁልጊዜ በየትኛውም ሆነ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ በእርሱ ታመኑ።**

መዝ. 62:5-8። ነፍሴ ሆይ፣ ዐርፈሽ እግዚአብሔርን ብቻ ጠብቂ፤ ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ነውና፡ ዐለቴና መድኀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤ መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ እኔም አልናወጥም። መዳኔና ክብሬ በእግዚአብሔር ነው፤ ብርቱ ዐለቴና መሸሸጊያዬ በእግዚአብሔር ነው። ሰዎች ሆይ፤ ሁልጊዜ በእርሱ ታመኑ፤ ልባችሁን በፊቱ አፍስሱ፤ እግዚአብሔር መጠጊያችን ነውና።

**30. እግዚአብሔር፣ በሚፈሩትና በማይለወጠው ፍቅሩ ላይ በሚተማመኑ ሰዎች ይደሰታል።**

መዝ. 147:11። ነገር ግን እግዚአብሔር በሚፈሩት፣ በምሕረቱ በሚታመኑትም ይደሰታል።

**31. ምንም እንኳ የተመኛችሁት በረከት ከእናንተ የራቀና የዘገየ ቢመስላችሁም፣ በእግዚአብሔር የማይለወጥ ፍቅር ላይ መታመናችሁን ቀጥሉ።**

መዝ. 13።

መዝ. 13:1። እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከ መቼ ድረስ ለዘላለሙ ትረሳኛለህ? ፊትህንስ ከእኔ የምትሰውረው እስከ መቼ ድረስ ነው?

መዝ. 13:5-6። እኔ ግን በጸናች ፍቅርህ እታመናለሁ፤ ልቤም በማዳንህ ደስ ይለዋል። ቸርነቱ በዝቶልኛልና፣ ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ።

**32. የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ ጉዞአቸው ወቅት በድንቅ ቢመራቸውም እንኳ፣ ወደ ተስፋው ምድር**



**በሰላም እንደሚያደርሳቸው ስላላመኑ ተገሠጹ፣ ተፈረደባቸው።**

ዘዳ. 1:26-36።

ዘዳ. 1:32-33። ይህም ሆኖ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም) አልታመናችሁም፤ በጉዞ ላይ ሳላችሁ የምትሰፍሩባቸውን ቦታዎች ለመፈለግና የምትሄዱበትን መንገድ ለማሳየት እርሱ ሌሊት በእሳት፣ ቀን በደመና ይመራችሁ ነበር።

# ማስጠንቀቂያዎች፣
# የንስሐና የመታዘዝ ጥሪዎች

በተጨማሪ ንስሐን በገጽ 186፣ መታዘዝን በገጽ 136 ላይ ተመልከቱ።

ማስታወሻ፡- እግዚአብሔርን ለሚታመኑትና በታማኝነት ለሚያገለግሉት ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ከበረከቶች ጋር ተጣምረው ቀርበውላቸዋል።

**1. የኀጢአት መንገድ ወደ ሞት ይመራል፤ የመታዘዝ መንገድ ግን ወደ ሕይወት ይመራል።**

ማቴ. 7:13-14። በጠባቡ በር ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ትልቅ፣ በሩም ሰፊ ነውና፤ ብዙዎችም በዚያ ይገባሉ። ወደ ሕይወት የሚያደርሰው ግን መንገዱ ቀጭን፣ በሩም ጠባብ ነው፤ የሚገቡበትም ጥቂቶች ብቻ ናቸው።

**2. የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰሙትና የሚታዘዙት ብቻ ሕይወት ያገኛሉ።**

ማቴ. 7:21-23። በሰማይ ያለውን ያባቴን ፈቃድ ሳይፈጽም <ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤> የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማይ አይገባም። በዚያ ቀን ብዙዎች፣ <ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ፤ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ታምራት አላደረግንምን?> ይሉኛል። በዚያ ጊዜ፣ <ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንት ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ!> ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ።

**3. ኢየሱስ የብልኅንና የሞኙን ቤት ሠሪዎች ምሳሌ ሰጥቶናል።**

ማቴ. 7:24-27። «እንግዲህ ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል፤ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራን ብልኅ ሰው ይመስላል። ዶፍ ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንንም ቤት መታው፤ በዐለት መሠረትም ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም። ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራን ሞኝ ሰው ይመስላል። ዶፍ ወረደ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንን ቤት መታው፤ ቤቱም ወደቀ፤ አወዳደቁም የከፋ ነበር።»



**4. የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ።**

ምሳ. 22:5። በክፉዎች መንገድ ላይ እሾህና ወጥመድ አለ፤ ነፍሱን የሚጠብቅ ግን ከእነዚህ ይርቃል።

ምሳ. 11:19-21። እውነተኛ ጻድቅ ሕይወትን ያገኛል፤ ክፋትን የሚከተል ግን ወደ ሞቱ ይጓዛል። እግዚአብሔር ልበ ጠማሞችን ይጸየፋል፤ በመንገዳቸው ነቀፋ በሌለባቸው ሰዎች ግን ደስ ይሰኛል። ክፉ ሳይቀጣ እንደማይቀር ዕወቅ፤ ጻድቃን ግን በነጻ ይሄዳሉ።

ገላ. 6:7-8። አትታለሉ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳል። ሥጋዊ ምኞቱን ለማርካት የሚዘራ፣ ከሥጋ ጥፋትን ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ግን ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።

**5. ማንም ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም። እግዚአብሔር ቅይጥ ሕይወት አይቀበልም።**

ማቴ. 6:24። አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን ይንቃል። እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም።

**6. እግዚአብሔር በኃጢአት ውስጥ የሚገኘውን ሰው አምልኮ አይቀበልም።**

ምሳ. 15:8። እግዚአብሔር የክፉዎችን መሥዋዕት ይጸየፋል፤ የቅኖች ጸሎት ግን ደስ ያሰኘዋል።

ምሳ. 15:29። እግዚአብሔር ከክፉዎች ሩቅ ነው፤ የጻድቃንን ጸሎት ግን ይሰማል።

ምሳ. 21:27። የክፉ ሰው መሥዋዕት አጸያፊ ነው፤ በክፉ ዐላማ ሲያቀርብማ የቱን ያህል አስከፊ ይሆን!

ምሳ. 28:9። ሕግን ላለመስማት ጆሮውን የሚደፍን፣ ጸሎቱ እንኳ አስጸያፊ ነው።

**7. እግዚአብሔር የሚሰጥህን የንስሐ ጥሪ ችላ ብትል፣ እግዚአብሔር በጥፋትህ ላይ ይስቃል።**

ምሳ. 1:24-33::

8. እግዚአብሔር ክፉዎችን ይረግማል፣ ጻድቃንን ግን ይባርካል::

ምሳ. 3:33:: የእግዚአብሔር ርግማን በክፉዎች ቤት ላይ ነው፤ የጻድቃንን ቤት ግን ይባርካል::

9. የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው::

ሮሜ 6:23:: የኀጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው::

10. ከጌታ እንዳንወሰድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል::

ዕብ. 2:1-3:: ስለዚህ ከሰማነው ነገር ስተን እንዳንወድቅ፣ ለሰማነው ነገር አብልጠን ልንጠነቀቅ ይገባናል:: ምክንያቱም በመላእክት በኩል የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነና ማንኛውም መተላለፍና አለመታዘዝ ተገቢውን ቅጣት ከተቀበለ፣ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ ድነት ቸል ብንል እንዴት ልናመልጥ እንችላለን? ይህ ድነት በመጀመሪያ በጌታ ተነገረ፤ ከእርሱ የሰሙትም ለእኛ አረጋገጡልን::

11. እንዳንወድቅ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል::

ዕብ. 6:4-6:: አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፣ ሰማያዊውን ስጦታ የቀመሱትን፣ ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች የሆኑትን፣ መልካሙን የእግዚአብሔር ቃልና የሚመጣውን ዓለም ኀይል የቀመሱትን፣ በኋላ ግን የካዱትን እንደገና ወደ ንስሓ መመለስ አይቻልም፤ ምክንያቱም እነርሱ ለገዛ ጥፋታቸው የእግዚአብሔርን ልጅ እንደገና ይሰቅሉታል፤ ያዋርዱታልም::

12. እውነትን አውቀው ኃጢአት ማድረግን የሚቀጥሉ ሰዎች ቅጣቱን እንደሚቀበሉ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል::

ዕብ. 10:26-31::

ዕብ. 10:26-27:: የእውነትን ዕውቀት ከተቀበልን በኋላ ሆን ብለን በኀጢአት ጸንተን ብንመላለስ፣ ከእንግዲህ ለኀጢአት የሚሆን ሌላ መሥዋዕት አይኖርም፤ የሚቀረው ግን የሚያስፈራ ፍርድና



የእግዚአብሔርን ጠላቶች የሚበላ ብርቱ እሳት መጠበቅ ብቻ ነው::

ዕብ. 10:31:: በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ እጅግ የሚያስፈራ ነው::

13. ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ፤ ዛሬ ድምፁን ስሙ::

ዕብ. 3:7-15::

ዕብ. 3:7-8:: ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፣ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፤ በምድረ በዳ በፈተና ቀን፣ በዐመፅ እንዳደረጋችሁት፣ ልባችሁን አታደንድኑ::

14. በፍርድ ቀን ኢየሱስ በጎቹን ከፍየሎች ይለያል::

ማቴ. 25:31-46::

ማቴ. 25:34:: በዚያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ በኩል ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፤ «እናንተ አባቴ የባረካችሁ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ::»

ማቴ. 25:41:: ከዚያም በግራው በኩል ላሉት ደግሞ እንዲህ ይላቸዋል፤ «እናንተ የተረገማችሁ፤ ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀው የዘላለም እሳት ከእኔ ተለይታችሁ ሂዱ::»

ማቴ. 25:46:: እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ::

15. ዓለምን ሁሉ ብታተርፍና ነፍስህን ግን ብታጐድል ምን ይጠቅምሃል?

ማቴ. 16:26-27:: ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ፣ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው በነፍሱ ምትክ ሊከፍለው የሚችለው ዋጋ ምንድን ነው? የሰው ልጅ በአባቱ ክብር ከመላእክት ጋር ይመጣል፤ ለእያንዳንዱም ሰው እንደ ሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል::

16. ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለን::

2ኛ ቆሮ. 5:10:: ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለንና፤ እያንዳንዱም ሰው በሥጋው ለሠራው በጎ ወይም ክፉ

ሥራ ተገቢውን ዋጋ ይቀበላል።»

17. ሁል ጊዜ ለኢየሱስ መመለስ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ። ምክንያቱም ቀኑና ሰዓቱ አይታወቁም።

ማር. 13:32-37። «ነገር ግን ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያችም ሰዓት ከአብ በቀር፣ የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን ማንም አያውቅም። ስለዚህ ጊዜው መቼ እንደሚሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፣ ጸልዩም። ይህም ቤቱን ለአገልጋዮቹ ትቶ፣ እያንዳንዱን አገልጋይ በየሥራ ድርሻው ላይ አሰማርቶ፣ በረኛው ነቅቶ እንዲጠብቅ አዝዞ የሄደውን ሰው ይመስላል። እንግዲህ የቤቱ ባለቤት በምሽት ወይም በውድቅት፣ በዶሮ ጩኸት ወይም ጎሕ ሲቀድ እንደሚመጣ አታውቁምና ተግታችሁ ጠብቁ፤ ድንገት ሲመጣ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ! ለእናንተ የምነግራችሁን ለሰው ሁሉ እናገራለሁ፤ ተግታችሁ ጠብቁ!»

18. ኢየሱስ አሥሩን ቆነጃጅት ምሳሌ ሰጠን።

ማቴ. 25:1-13።

19. በኢየሱስ የሚያምኑ ብቻ ይድናሉ።

ዮሐ. 3:16-18። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፤ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው። በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ፣ አሁኑኑ ተፈርዶበታል።»

20. በክፉዎች ምክር የማይሄድ ሰው ምስጉን ነው። ክፉዎች በፍርድ ቀን መቆም አይችሉም።

መዝ. 1።

21. እግዚአብሔር ያመጣው የጥፋት ውኃና የሰዶምና የገሞራ ጥፋት ለዛሬዎቹ አማኞች እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኖ ቀርቧል።

2ኛ ጴጥ. 2:4-10።



ይሁዳ 6-7፤ 14-15።

22. የሌሎች ሰዎች ታሪክ ለእኛ እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኖ ተጽፎልናል።

1ኛ ቆሮ. 10:11-12። ይህ ሁሉ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በእነርሱ ላይ ደረሰ፤ የዘመናት ፍጻሜ የደረሰብንን እኛን ለማስጠንቀቅም ተጻፈ። ስለዚህ ተደላድዬ ቆሜአለሁ የሚል ቢኖር እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።

23. እግዚአብሔር በደለኞችን ይቀጣል።

ናሆም 1:1-6።

ናሆም 1:2-3። እግዚአብሔር ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር የሚበቀል፣ በመዓትም የተሞላ ነው። እግዚአብሔር ባላጋራዎቹን ይበቀላል፤ በጠላቶቹም ላይ ቍጣውን ያመጣል። እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ በኀይሉም ታላቅ ነው፤ እግዚአብሔር በደለኛውን ሳይቀጣ አያልፍም፤ መንገዱ በዐውሎ ነፋስና በማዕበል ውስጥ ነው፤ ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው።

24. ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ ለሚሉ ሰዎች ወዮላቸው።

ኢሳ. 5:20-21። ክፉውን መልካም፣ መልካሙን ክፉ ለሚሉ ብርሃኑን ጨለማ፣ ጨለማውን ብርሃን ለሚያደርጉ፣ ጣፋጩን መራራ፣ መራራውንም ጣፋጭ ለሚያደርጉ ወዮላቸው! ራሳቸውን እንደ ብልኅ ለሚቈጥሩ በራሳቸውም አመለካከት ጥበበኛ ለሆኑ ወዮላቸው!

25. መንገዱን የሚያውቅና ከእግዚአብሔር ፊቱን የሚያዞር ትልቅ ፍርድን ይቀበላል።

2ኛ ጴጥ. 2:20-22። ጌታችንንና አዳኛችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ከዓለም ርኩሰት ካመለጡ በኋላ እንደ ገና ተጠላልፈው ቢሸነፉ ከመጀመሪያው ይልቅ የኋለኛው ሁኔታቸው የከፋ ይሆንባቸዋል። የጽድቅን መንገድ ካወቁ በኋላ ከተሰጣቸው ቅዱስ ትእዛዝ ወደ ኋላ ከሚመለሱ፣ ቀድሞውኑ የጽድቅን መንገድ ባላወቁት ይሻላቸው ነበር። «ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል» እንዲሁም «ዐሣማ ቢታጠብም ተመልሶ በጭቃ ላይ ይንከባለላል»

የሚለው ምሳሌ እውን ይሆንባቸዋል።

**26. ንስሐ ያልተገባበት ኀጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ይለያል።**

ኢሳ. 59:1-2። እነሆ፤ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፤ ጆሮውም መስማት አልተሳናትም። ነገር ግን በደላችሁ ከአምላካችሁ ለይቶአችኋል፤ ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል፤ በዚህም ምክንያት አይሰማም።

**27. እግዚአብሔር የግብዝነት አምልኮንና የዓለማዊነትን ሕይወት ጥምረት ይጸየፋል።**

ኤር. 7:1-29።

ኤር. 7:2-4። «በእግዚአብሔር ቤት በር ቁም፤ በዚያም ይህን መልእክት ዐውጅ፤ «እግዚአብሔርን ለማምለክ፣ በእነዚህ በሮች የምትገቡ የይሁዳ ሕዝብ ሁላችሁ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ። የእስራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ «መንገዳችሁንና ሥራችሁን አስተካክሉ፤ እኔም በዚህ ስፍራ እንድትኖሩ አደርጋችኋለሁ። ይህ <የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፣ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ> ነው። እያላችሁ በሐሰት ቃል አትታመኑ።»

ኤር. 7:9-11። «ትሰርቃላችሁ፤ ሰው ትገድላላችሁ፤ ታመነዝራላችሁ፤ በሐሰት ትምላላችሁ፤ ለበኣል ታጥናላችሁ፤ የማታውቋቸውንም ሌሎች አማልክት ትከተላላችሁ፤ ስሜ ወደሚጠራበት ወደዚህ ቤት መጥታችሁ በፊቴ ትቆሙና «ደህና ነን»። እያላችሁ እነዚህን አስጸያፊ ነገሮች ታደርጋላችሁ። ስሜ የሚጠራበት፣ ይህ ቤት በእናንተ ዘንድ የወንበዴዎች ዋሻ ሆኖአልን? እነሆ፤ የምታደርጉትን ነገር አይቻለሁ! ይላል እግዚአብሔር።»



# ሥራ፣ ስንፍና

1. **በታሪክ መጀመሪያ ላይ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንደ ራሱ አገልጋይ ሆኖ እንዲሠራ ጠራው።**

ዘፍ. 2:15። እግዚአብሔር አምላክ (ያህዌ ኤሎሂም) ሰውን ወስዶ እንዲያለማለትና እየተንከባከበ እንዲጠብቃት በዔድን የአትክልት ስፍራ አስቀመጠው።

2. **በእግዚአብሔር የተመሰከረልህ ሠራተኛ ሁን።**

2ኛ ጢሞ. 2:15። እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሠከረለት ሠራተኛ፤ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።

3. **ሁሉንም ነገሮች ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ፤ ሥራህን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መልኩ አከናውን።**

1ኛ ቆሮ. 10:31። እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።

ቆላ. 3:17። በእርሱ በኩል ለእግዚአብሔር አብ ምስጋና እያቀረባችሁ፣ በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት።

4. **ታታሪ የሆነች የቤት እመቤትና እናት ጌታንና ባልዋን ደስ ታሰኛለች።**

ምሳ. 31:10-31።

5. **ክርስቲያኖች ለሌሎች ያካፍሉ ዘንድ መሥራት አለባቸው፤ በጭራሽ መስረቅ አይገባቸውም።**

ኤፌ. 4:28። ይሰርቅ የነበረ ከእንግዲህ አይስረቅ፤ ነገር ግን ለተቸገሩት የሚያካፍለው ነገር እንዲኖረው በገዛ እጆቹ በጎ የሆነውን እየሠራ ለማግኘት ይድከም።

6. **በውጭ ላሉት ጥሩ ምስክር መሆን እንድትችል ታማኝ ሠራተኛ ሁን፣ እንዲሁም የሌሎች ጥገኛ አትሁን።**

1ኛ ተሰ. 4:11-12:: ከዚህ በፊት እንዳዘዝናችሁ በገዛ እጃችሁ ሥሩ፤ በጸጥታ ኑሩ፤ በራሳችሁ ጉዳይ ላይ ብቻ አተኩሩ:: ይኸውም በዕለት ተለት ኑሮአችሁ በውጭ ባሉት ዘንድ እንዲያስከብራችሁና በማንም ሰው ላይ ሸክም እንዳትሆኑ ነው::

**7. ሥራ ፈት እንዳትሆኑ ተጠንቀቁ::**

2ኛ ተሰ. 2:6-15::

2ኛ ተሰ. 3:7-10:: የእኛን ምሳሌ እንዴት መከተል እንደሚገባችሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁና:: ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ ሥራ ፈቶች አልነበርንም፤ ደግሞም የማንንም እንጀራ በነጻ አልበላንም፤ ነገር ግን ከእናንተ በአንዳችሁም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እንደክምና እንሠራ ነበር፤ ይህን ያደረግነው ምሳሌነታችንን እንድትከተሉ ብለን እንጂ የሚያስፈልገንን ነገር ከእናንተ ለማግኘት ሥልጣን ሳይኖረን ቀርቶ አይደለም:: ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ፣ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» ብለን ይህን ትእዛዝ ሰጥተናችሁ ነበርና::

**8. የራሳችሁን እንጀራ ተቀበሉ::**

2ኛ ተሰ. 3:12:: እንደዚህ ያሉ ሰዎች ተግተው ሥራቸውን እንዲሠሩና እንጀራቸውን እንዲበሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛቸዋለን፤ እንመክራቸዋለንም::

**9. ጉንዳን ለሰነፎችና ለግድ የለሾች ትምህርት ትሰጣቸዋለች::**

ምሳ. 6:6-11:: አንተ ታካች፤ ወደ ጉንዳን ሂድ፤ ዘዴውን አስተውለህ ጠቢብ ሁን፤ አዛዥ የለውም፤ አለቃም ሆነ ገዥ የለውም፤ ሆኖም ግን በበጋ ምግቡን ያከማቻል፤ በመከርም ወቅት ቀለቡን ይሰበስባል:: አንተ ታካች፣ እስከ መቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ? ጥቂት ማንቀላፋት፤ ጥቂት ማንጐላቸት፤ እጅን አጣጥፎ «እስቲ ጥቂት ልረፍ» ማለት፤ ድኽነት እንደ ወንበዴ፣ ዕጦትም መሣሪያ እንደ ታጠቀ ሰው ከተፍ ይልብሃል::

**10. ሰነፍ መሆን ውርደት ነው::**

ምሳ. 10:5:: ሰብሉን በበጋ የሚሰበስብ ጠቢብ ልጅ ነው፤



በመከር ጊዜ የሚተኛ ግን ውርደት ይከተለዋል::

**11. ሊሆን የማይችል ነገርን የሚያሳድድ ማመዛዘን አይችልም::**

ምሳ. 12:11:: መሬቱን የሚያርስ የተትረፈረፈ ምግብ ያገኛል፤ ከንቱ ተስፋን የሚያሳድድ ግን ማመዛዘን ይጐድለዋል::

**12. ተራ ወሬ ወደ ድኽነት ይመራል::**

ምሳ. 14:23:: ለፍተው የሠሩት ሁሉ ትርፍ ያስገኛል፤ ከንቱ ወሬ ግን ወደ ድኽነት ያመራል::

**13. የሰነፍ መንገድ አዳጋች ነው::**

ምሳ. 15:19:: የሀኬተኛ መንገድ በእሾህ የታጠረች ናት፤ የቅኖች መንገድ ግን የተጠረገ አውራ ጐዳና ነው::

**14. ዋልጌ ሰው ይራባል::**

ምሳ. 19:15:: ስንፍና ከባድ እንቅልፍ ላይ ይጥላል፤ ዋልጌም ሰው ይራባል::

**15. ሰነፍ መሆን አሳዛኝ ውጤት አለው::**

ምሳ. 20:4:: ሰነፍ ሰው በወቅቱ አያርስም፤ ስለዚህ በመከር ወራት ይፈልጋል፤ አንዳችም አያገኝም::

**16. እንቅልፍን አትውደዱ::**

ምሳ. 20:13: እንቅልፍ አትውደድ፤ አለዚያ ድኻ ትሆናለህ፤ ዐይንህን ክፈት፤ የተትረፈረፈ ምግብ ይኖርሃል::

**17. ዋልጌ ሰነፍ ድኻ ይሆናል::**

ምሳ. 24:30-34:: በሰነፍ ሰው ዕርሻ በኩል አለፍሁ፤ ማስተዋል የጐደለውን ሰው የወይን ቦታ አልፌ ሄድሁ፤ በያለበት እሾህ በቅሎበታል፤ መሬቱም ዐረም ለብሶአል፤ ቅጥሩም ፈራርሷል:: ያየሁትን ነገር አወጣሁ አወረድሁ፤ ካስተዋልሁትም ትምህርት አገኘሁ፤ «ጥቂት ላንቀላፋ፣ ጥቂት ላሸልብ፣ እጄን አጣጥፌ ጥቂት ልረፍ» ብትል፣ ድኽነት እንደ ወንበዴ፣ እጦትም እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል::

**18. ሰነፍ ላለመሥራት ምክንያትን ይፈልጋል፤ ስለ ባሕሪውም ምክንያት ይሰጣል።**

ምሳ. 26:13-16፡፡ ሰነፍ፣ «በመንገድ ላይ አንበሳ አለ፤ አስፈሪ አንበሳ በአውራ ጐዳና ላይ ይጐማለላል» ይላል፡፡ መዝጊያ በማጠፊያው ላይ እንደሚዞር፣ ሰነፍም በዐልጋው ላይ ይገላበጣል፡፡ ሰነፍ እጁን ወጭት ውስጥ ያጠልቃል፤ ወደ አፉ ለመመለስ ግን እጅግ ይታከታል፡፡ በማስተዋል መልስ ከሚሰጡ ከሰባት ሰዎች ይልቅ፣ ሰነፍ ራሱን ጠቢብ አድርጎ ይቈጥራል፡፡

**19. የትጉሕ ሠራተኛ እንቅልፍ የጣፈጠ ነው።**

መክ. 5:12፡፡ ጥቂትም ይሁን ብዙ ቢበላ፣ የሠራተኛ እንቅልፍ ጣፋጭ ነው፤ የሀብታም ሰው ብልጽግና ግን እንቅልፍ ይነሣዋል፡፡

**20. በመክሊቶቹ ምሳሌ ኢየሱስ፣ እኛም በተሰጡን መክሊቶች በታማኝነት እንድናገለግለው ያስተምረናል።**

ማቴ. 25:14-30፡፡

**21. ለገዛ ቤተሰቦቹ የማያስብ ሰው ሃይማኖትን የካደ ነው።**

1ኛ ጢሞ. 5:8፡፡ አንድ ሰው ዘመዶቹን፣ በተለይም የቅርብ ቤተ ሰቡን የማይረዳ ከሆነ ሃይማኖቱን የካደ፣ ከማያምንም ሰው ይልቅ የባሰ ክፉ ነው፡፡

**22. የዕለት ተዕለት ፍላጐቶቻችንን ለማሟላትና ውጤታማ ኑሮ ለመኖር፣ ሥራ መሥራትን መማር አለብን።**

ቲቶ 3:14፡፡ ከእኛ ወገን ለሆኑት ለዕለት የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙና ኑሮአቸውም ፍሬ የሌለው እንዳይሆን ለመልካም ሥራ መትጋትን ይማሩ ዘንድ ይገባቸዋል፡፡



# ስጋት፣ ጭንቀት

በተጨማሪ ጸሎትን በገጽ 166 ላይና መታመንን በገጽ 224 ላይ ተመልከት፡፡

**1. ኢየሱስ ስለ ነገ፣ ስለ ምግብና ልብስ፣ እንዳንጨነቅ አስተምሮናል።**

ማቴ. 6:25-34፡፡

ማቴ. 6:25፡፡ ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ኑሮአችሁ ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? በማለት አትጨነቁ፡፡ ሕይወት ከምግብ፣ ሰውነትስ ከልብስ አይበልጥምን?

ማቴ. 6:26፣ 28፡፡ እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፣ አይዘሩም፣ አያጭዱም፤ በጐተራም አያከማቹም፤ ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል፡፡ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? . . . ደግሞስ ስለ ልብስ ለምን ትጨነቃላችሁ? እስቲ የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ፤ አይለፉም፤ ወይም አይፈትሉም፡፡

**2. በአንድ ጊዜ በአንድ ቀን ተወሰኑ፣ ችግርን አትበደሩ።**

ማቴ. 6:34፡፡ ስለዚህ ለነገ በማሰብ አትጨነቁ፤ የነገ ጭንቀት ለነገ ይደር፤ እያንዳንዱ ዕለት የራሱ የሆነ በቂ ችግር አለው፡፡

**3. አትጨነቁ፣ ግን ጸልዩ።**

ፊል. 4:6-7፡፡ በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ፣ ከምስጋናም ጋር ልመናችሁን በእግዚአብሔር ፊት አቅርቡ እንጂ ስለ ማንኛውም ነገር አትጨነቁ፡፡ ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል፡፡

**4. የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በጌታ ላይ ጣሉ።**

1ኛ ጴጥ. 5:6-7፡፡ ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት፡፡

**5. የሰላምና የጸጥታን ምሥጢር ልታገኙ ትችላላችሁ።**

መዝ. 37:3-7::

መዝ. 37:3:: በእግዚአብሔር ታመን፣ መልካምንም አድርግ::

መዝ. 37:4:: በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ::

መዝ. 37:5:: መንገድህን ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ::

መዝ. 37:7:: በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል::

**6. ጭንቀት ሰውን ይጫጫነዋል::**

ምሳ. 12:25:: ሥጉ ልብ ሰውን በሐዘን ይወጥራል፤ መልካም ቃል ግን ደስ ያሰኘዋል::

ምሳ. 14:30:: ሰላም ያለው ልብ ለሰውነት ሕይወት ይሰጣል፤ ቅናት ግን ዐጥንትን ያነቅዛል::

ምሳ. 17:22:: ደስተኛ ልብ ጥሩ መድኀኒት ነው፤ የተሰበረ መንፈስ ግን ዐጥንትን ያደርቃል::



# ወጣትነት

በተጨማሪ የኃጢአት ይቅርታን በገጽ 90 ላይ፣ ጓደኝነትን በገጽ 102፣ እንዲሁም ማስጠንቀቂያዎችን በገጽ 232 ላይ ተመልከቱ::

**1. አንተ ወጣት፣ ደስ ይበልህ::**

መክ. 11:9-10:: አንተ ወጣት በወጣትነትህ ጊዜ ደስ ይበልህ፤ በወጣትነትህም ዘመን ልብህ ደስ ያሰኝህ፤ የልብህን መንገድ፣ ዐይንህ የሚያየውንም ሁሉ ተከተል፤ ነገር ግን ስለ እነዚህ ነገሮች ሁሉ፣ እግዚአብሔር ወደ ፍርድ እንደሚያመጣህ ዕወቅ:: ስለዚህ ጭንቀትን ከልብህ አርቅ፤ ክፉ ነገርንም ከሰውነትህ አስወግድ፤ ወጣትነትና ጉብዝና ከንቱ ናቸውና::

**2. በወጣትነትህ ዘመን ፈጣሪህን አስብ::**

መክ. 12:1:: የጭንቀት ጊዜ ሳይመጣ፣ «ደስ አያሰኙኝም» የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ፣ በወጣትነትህ ጊዜ፣ ፈጣሪህን አስብ::

**3. በእግዚአብሔር መንገድ ላይ መሄድህን አረጋግጥ::**

ምሳ. 3:1-4:: ልጄ ሆይ፤ ትምህርቴን አትርሳ፤ ትእዛዛቴን በልብህ ጠብቅ፤ ቀኖችን ይጨምሩልሃል፤ ዓመቶችንም ያረዝሙልሃል፤ ሕይወት፣ ሀብትንና ሰላምን ያበዙልሃል:: ፍቅርና ታማኝነት ከቶ አይለዩህ፤ በዐንገትህ ዙሪያ እሰራቸው፤ በልብህም ጽላት ላይ ጻፋቸው:: በዚያን ጊዜ ሞገስንና መልካም ስምን፣ በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ታገኛለህ::

**4. በእግዚአብሔር ታመን፤ በመንገድህም ሁሉ እርሱን እወቅ::**

ምሳ. 3:5-6: በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን ዕወቅ፤ እርሱም ጐዳናህን ቀና ያደርገዋል::

**5. እግዚአብሔርን መፍራት የእውቀትና የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው::**

ምሳ. 1:7:: እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት መጀመሪያ ነው፤

ተላሎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ::

ምሳ. 9:10-11:: የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው፤ ዘመንህ በእኔ ምክንያት ይረዝማልና፤ ዕድሜም በሕይወትህ ላይ ይጨመርልሃል::

ምሳ. 15:33:: እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብን መማር ነው፤ ትሕትናም ክብርን ትቀድማለች::

**6. ሞኞች ትምህርትን ይንቃሉ::**

ምሳ. 1:7:: እግዚአብሔርን መፍራት የዕውቀት መጀመሪያ ነው፤ ተላሎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ::

ምሳ. 13:13:: ምክርን የሚያቃልል በራሱ ላይ ጥፋት ያመጣል፤ ትእዛዝን የሚያከብር ግን ወሮታን ይቀበላል::

**7. መልካም እንዲሆንልህ የወላጆችህን ምክር አድምጥ::**

ምሳ. 1:8-9:: ልጄ ሆይ፤ የአባትን ምክር አድምጥ፤ የእናትህንም ትምህርት አትተው:: ለራስህ ሞገስን የሚያጐናጽፍ አክሊል፣ ዐንገትህን የሚያስውብ ድሪ ይሆንልሃል::

ምሳ. 4:1-4:: ልጆቼ ሆይ፤ የአባትን ምክር አድምጡ፤ ልብ ብላችሁ ስሙ፤ ማስተዋልንም ገንዘብ አድርጉ:: በጎ ትምህርት እሰጣችኋለሁ፤ ስለዚህ ትምህርቴን አትተዉ:: በአባቴ ቤት ገና ለግላጋ ወጣት፣ ለእናቴም አንድ ልጇ ብቻ በነበርሁ ጊዜ፣ አባቴ እንዲህ ሲል አስተማረኝ፤ «ቃሌን በሙሉ በልብህ ያዝ፤ ትእዛዜንም ጠብቅ፣ በሕይወት ትኖራለህ::»

ምሳ. 6:20-24:: ልጄ ሆይ፤ የአባትህን ትእዛዝ አክብር፤ የእናትህንም ትምህርት አትተው:: ምንጊዜም በልብህ አኑራቸው፤ በአንገትህም ዙሪያ እሰራቸው:: በምትሄድበት ሁሉ ይመሩሃል፤ በምትተኛበት ጊዜ ይጠብቁሃል፤ በምትነቃበት ጊዜም ያነጋግሩሃል:: እነዚህ ትእዛዞች መብራት ናቸውና፤ ይህችም ትምህርት ብርሃን፣ የተግሣጽ እርምትም የሕይወት መንገድ ናት፤ እርሷም ከምግባረ ብልሹ ሴት፣ ልዝብ አንደበት ካላት ዘልዛላ ሴት ትጠብቅሃለች::»

**8. የጌታን ቅጣት አትናቅ፣ ምክንያቱም የሚወዳቸውን ይቀጣቸዋል**



**(ወላጆችም የእርሱን ምሳሌ መከተል አለባቸው::)**

ምሳ. 3:11-12:: ልጄ ሆይ፤ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አትናቅ፤ በዘለፋውም አትመረር፤ አባት ደስ የሚሰኝበትን ልጁን እንደሚቀጣ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም የሚወደውን ይገሥጻልና::

ዕብ. 12:5-11::

**9. እርማትን የሚጠላ ደነዝ ነው::**

ምሳ. 12:1:: ተግሣጽን የሚወድ ዕውቀትን ይወዳል፤ መታረምን የሚጠላ ግን ደነዝ ነው::

**10. ተግሣጽን ቸል አትበል፤ ስለ እርሱ አመስግን::**

ምሳ. 13:18:: ተግሣጽን የሚንቅ ወደ ድኽነትና ኀፍረት ይሄዳል፤ እርምትን የሚቀበል ሁሉ ግን ይከበራል::

ምሳ. 15:5:: ተላላ የአባቱን ምክር ይንቃል፤ መታረምን የሚቀበል ግን አስተዋይነቱን ያሳያል::

ምሳ. 15:12:: ፌዘኛ መታረምን ይጠላል፤ ጠቢባንንም አያማክርም::

ምሳ. 15:31-32:: ሕይወት ሰጪ የሆነውን ተግሣጽ የሚሰማ፣ በጠቢባን መካከል ይኖራል:: ተግሣጽን የሚንቅ ራሱን ይንቃል፤ እርምትን የሚቀበል ግን ማስተዋልን ያገኛል::

**11. ፍቅር ተግሣጽን ይጠይቃል::**

ምሳ. 13:24:: በአርጩሜ ከመቅጣት የሚሳሳለት ልጁን ይጠላል፤ የሚወደው ግን በጥንቃቄ ይቀጣዋል::

**12. ሌሎች ቢያባብሉህ፣ አትስማቸው ወይም እሺ አትበላቸው::**

ምሳ. 1:10-19::

ምሳ. 1:10:: ልጄ ሆይ፤ ኀጢአተኞች ቢያባብሉህ እሺ አትበላቸው::

ምሳ. 1:15:: ልጄ ሆይ፤ አብረሃቸው አትሂድ፤ በሚሄዱበትም መንገድ እግርህን አታንሣ::

**13. የክፉዎችን መንገድ አትከተል፤ ከእርሱም ሽሽ::**

ምሳ. 4:14-15:: ወደ ኀጥአን ጐዳና እግርህን አታንሣ፤ በክፉ ሰዎች መንገድ አትሂድ፤ ከዚያ አትድረስ፤ አትጓዝበት፤ ሽሸው፤ መንገድህን ይዘህ ሂድ::

**14. ጸንታችሁ ቁሙ፤ ወዲያ ወዲህ አትበሉ፤ አትወሰዱ::**

1ኛ ቆሮ. 15:58:: ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ:: ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ::

**15. የኢየሱስ ክርስቶስ ጀግና ወታደር ሁን፤ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ተጠቀም::**

ኤፌ. 6:10-18::

ኤፌ. 6:10-11:: በተረፈ በጌታና ብርቱ በሆነው ኀይሉ ጠንክሩ:: የዲያብሎስን የተንኰል ሥራ መቋቋም ትችሉ ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ ልበሱ::

**16. ወጣቱ ዮሴፍ ጥሩ ምሳሌአችን ነው::**

*ዘፍ. 39:: (ምንም እንኳን ዮሴፍ ከቤቱ ርቆ በግብፅ አገር ባሪያ ቢሆንም፣ በእምነትና በመንፈሳዊነት ጠንካራ ነበር:: ለጌታ መከራን ለመቀበል ዝግጁ ነበር፤ ይህንንም ኃጢአት ከመሥራት ይልቅ መረጠ:: የጲጢፋራ ሚስት በፈተነችው ጊዜ ለፍላጐቷ አልተገዛላትም ነበር::)*

ዘፍ. 39:9-10:: «በዚህ ቤት ላይ ከእኔ የበለጠ ኀላፊነት ያለው ማንም የለም፤ እርሱ ያልሰጠኝ ነገር ቢኖር፣ አንቺን ብቻ ነው፤ ያውም ሚስቱ ስለሆንሽ ነው፤ ታዲያ፣ እኔ ይህን ክፉ ድርጊት ፈጽሜ እንዴት በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት ኀጢአት እሠራለሁ?» ምንም እንኳ ዮሴፍን በየቀኑ ብትጐተጕተውም፣ አልሰማትም፤ ከእርሷ ጋር መተኛቱ ይቅርና አብሯትም መሆን አልፈቀደም::»

**17. ዳንኤልም ልንከተለው የሚገባን ጥሩ ምሳሌ ነው:: ወጣት ሆኖ ሳለ ወደ ባቢሎን ተወሰደ:: እዚያም ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆን የሚያስከፍለውን ዋጋ ሁሉ ከፈለ::**



ዳን. 1:8-9:: ዳንኤል ግን በንጉሡ ምግብና የወይን ጠጅ እንዳይረክስ ወሰነ፤ በዚህ መንገድ ራሱን እንዳያረክስም የጃንደረቦቹን አለቃ ፈቃድ ጠየቀው:: እግዚአብሔርም ለዳንኤል በጃንደረቦቹ አለቃ ፊት ሞገስንና መወደድን ሰጠው::

*ዳን. 6:: (ምንም እንኳን በአናብስት ዋሻ ውስጥ እንደሚጣል ቢያውቀውም፣ የንጉሡን ትእዛዝ በመተላለፍ ወደ እግዚአብሔር መጸለዩን ቀጠለ::)*

ዳን. 6:10:: ዳንኤልም ዐዋጁ እንደ ወጣ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ሄደ፤ መስኮቶቹ በኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው ባሉበት በሰገነቱ ቀድሞ ያደርግ እንደ ነበረው በቀን ሦስት ጊዜ ተንበርክኮ ጸለየ፤ አምላኩንም አመሰገነ::

**18. ሦስቱ የዳንኤል ጓደኞችም የሚያስከፍለውን ዋጋ በመክፈል ለእግዚአብሔር ታማኞች ሆኑ::**

ዳን. 3::

ዳን. 3:16-18:: ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብደናጎ ለንጉሡ እንዲህ ብለው መለሱ፤ «ናቡከደነፆር ሆይ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ ስለ ራሳችን መልስ መስጠት አያስፈልገንም:: ንጉሥ ሆይ፤ በሚንበለበለው የእቶን እሳት ውስጥ ብንጣል፣ የምናመልከው አምላክ ሊያድነን ይችላል፤ ከእጅህም ያድነናል:: ነገር ግን ንጉሥ ሆይ፤ ባያድነንም እንኳ፤ አማልክትህን እንደማናገለግል፣ ላቆምኸውም የወርቅ ምስል እንደማንሰግድ ዕወቅ::»

**19. አባትህንና እናትህን አክብር::**

ዘፀ. 20:12:: አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ (ያህዌ ኤሎሂም) በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም::

**20. ወላጆችህን አክብር፤ ታዘዛቸውም::**

ኤፌ. 6:1-3:: ልጆች ሆይ፤ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፤ ይህ ተገቢ ነውና:: «አባትህንና እናትህን አክብር» በሚለው ቀዳሚ ትእዛዝ ውስጥ ያለው ተስፋ፣ «መልካም እንዲሆንልህ፣ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም» [ዘዳ. 5:16] የሚል ነው::

ቈላ. 3:20:: ልጆች ሆይ፤ ይህ ጌታን ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ

ለወላጆቻችሁ በሁሉም ነገር ታዘዙ።

**21. ኢየሱስ ለወላጆቹ ታዛዥ ነበር።**

ሉቃ. 2:51። ከዚያም አብሮአቸው ወደ ናዝሬት ወረደ፤ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህን ሁሉ ነገር በልቧ ትጠብቀው ነበር።

**22. ከክፉ የወጣትነት ምኞት ሽሽ።**

2ኛ ጢሞ. 2:22። ከወጣትነት ክፉ ምኞት ሽሽ፤ በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋርም ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን ተከታተል።